# ምዕራፍ 7፥

## ቸ ንስሓ፥

**ንስሓ፥ <<ነስሐ ተፀፀተ>>** ብሎ ከግእዝ ግስ የሚገኝ ጥሬ ዘር ሲሆን፥ ንስሓን መግባት ማለትም፥ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ባጠፉት ጥፋት፣ በበደሉት በደል በተሳሳቱት ስሕተት ተፀፅተው፥ ከጥፋት፣ ከበደልና ከስሕተት ወደ እውነተኛ መንገድ መመለስ፥ ክፉ ዐመልንና መጥፎ ባሕርይን (ፀባይን) መተው፡ ወደክፉ ተግባር ላለመመለስም በቍርጥ ሐሳብ መወሰን ማለት ነው።

ንስሓ፥ በጾም፣ በጸሎትና በስግደት የሚከናወን ሱባኤ እንደመሆኑ መጠን፥ መንፈሳዊ ምሥጢሩና አፈጻጸሙ ሁሉ ከጾምና ከጸሎት ጋር የተያያዘ ነው።

ከዚህ ከፍ ብሎ በጾምና በጸሎት ክፍል የተገለጸውም በሙሉ ይመለከተዋል።

ንስሓ፥ በደሉን አምኖ ለሚናዘዝ ሰው እንደጥፋቱ፣ እንደበደሉና እንደስሕተቱ ከብደት እየታየ ሥልጣነ ክህነት ባላቸው የቤተ ክርስቲያናችን አባቶች ካህናት አማካይነት ምንም ልዩነት ሳይደረግ ለሁሉ የሚሰጥ፥ በምግባረ እከይ የተጣመመውን ሰው የሚያቀና፥

ከገቢረ ሠናይ (ከመልካም ምግባር) የጐደለውንም የሚሞላ፣ (ስርዋጽ) ተብሎ ሊጠራ የሚችል መንፈሳዊ ቅጣት ነው።

እዎ ንስሓ፥ ጥፋቱንና ስሕተቱን በትክክል አምኖ የሚናዘዝ፥ ከበደሉና ከስሕተቱ ሁሉ ተመልሶ ፈጣሪውን በንጹሕ ልብ የሚለምነውን ሰው ከአበሳው የሚያነጻ፣ ጻድቅንም የሚያደርግ፥

በማጠቢያ ሳሙና እና በንጹሕ ውሃ የሚመሰል የኃጢአት ዕድፍ ማስወገጃ መንፈሳዊ መሣሪያ ነው።

ንስሓ፥ በደሉን በሚናዘዝ ሰውና በካህኑ መካከል ብቻ የሚከናወን፣ ከእግዚአብሔር ይቅርታን የሚለመንበት፣ ከካህኑና ከተናዛዢው ሰው በስተቀር ማንም ሊያውቀው የማይገባው መንፈሳዊ ምሥጢር ነው።





ንስሓ፥ ምንም እንኳ በሐዲስ ኪዳን አፈጻጸሙ ሁሉ በሃይማኖታዊ ሥርዓት (በቀኖና ቤተ ክርስቲያን) ተለይቶ የተቀመጠና እየተሠራበት ያለ ቢሆንም፥ ቀደም ሲልም፥ ብዙ ሕዝብ በልዩ ልዩ ጥፋታቸው እየተፀፀቱ፣ በበደሉት በደል እያዘኑ፣ እያለቀሱ፣ ከስሕተታቸው ወደ እግዚአብሔር እየተመለሱ፥ ከፈጣሪአቸው ምሕረትንና ይቅርታን ሲለምኑበት የነበረ፥ የበደለኞችና የይቅር ባይ፣ የመሐሪው አምላክ እግዚአብሔር መገናኛ፣ ድልድይ፣ አስታራቂ፥ (ልዩ የሆነ መንፈሳዊ ሽማግሌ) መሆኑን ከቅዱሳት መጻሕፍት መረዳት እንችላለን።

## ክፍል 27፥

## ንስሓ፥ በብሉይ ኪዳን፥

ለምሳሌ ያህልም፥ ከላይ በጾም አንቀጽ በሰፊው እንደተገለጸው የነነዌ ሰዎች አመድ ነስንሰው፣ ድንጋይ ተንተርሰው፣ ማቅ ለብሰው እግዚአብሔርን በጾም፣ በጸሎትና በልቅሶ፥ በልዩ ሱባኤ ንስሓ ገብተው በለመኑት ጊዜ እግዚአብሔር ሰምቷቸዋል።

በበደላቸውና በጥፋታቸው ተፀፅተው ንስሓ ስለ ገቡ፥ ወደ እውነተኛው አምላካቸው ስለ ተመለሱ ከታዘዘባቸው መቅሠፍት ተርፈዋል።

ትንቢተ ዮናስን ከመጀመሪያው እንሥተን ብንመለከት ምሥጢሩን በሰፊው ያስረዳናል። ትንቢተ ዮናስ 1፥1, 3፥1።

እዎ ንስሓ የይቅርታ መጠየቂያ ልዩ ሞደል በመሆኑ የምሕረትና የርኅራኄ ባለቤት ፈጣሪአችን እግዚአብሔር በፍጹም ልባችን ንስሓ ገብተን፣ ባጠፋነው ጥፋት ተፀፅተን፣ ከስሕተት ወደ እውነት፣ ወደ እርሱ መመለስ እንደሚገባን፥ ይቅር እንዲለን፣ ከኃጢአታችን ሁሉ እንዲያነጻንም አምላካችንን በፍጹም ልባችን መለመን እንዳለብን፥ ደጋግሞ ነግሮናል።

ለምሳሌም፥ ኢዩኤል 2፥ ከቍጥር 1 ጀምሮ፥ በተለይም ቍጥር 12 ብንመለከት ይህን በሰፊው መረዳት እንችላለን።

ንስሓ ለምሳሌ ያህል ከዚህ በዐጭሩ የተገለጸ ሲሆን፥ በተጨማሪም ቅዱሳት መጻሕፍትን ቀስ ብለን በሰፊው

ብንመረምር መሠረታዊ አመጣጡና ጥቅሙ በብዙ ክፍል ተዘግቦ እናገኘዋለን። በተለይም ሕዝበ እስራኤል በዘመናቸው ሁሉ እግዚአብሔርን በሚያሳዝኑበት ጊዜ ልዩ ልዩ ቅጣት ይታዘዝባቸው ስለ ነበር፥ በንስሓ፣ በኀዘንና በልቅሶ ወደ እርሱ ተመልሰው ፈጣሪያቸውን ሲለምኑ ደግሞ ምሕረትንና ይቅርታን ያገኙ ነበር።

<u>መዝ 77፥1 ጀምሮ በተለይም ቍጥር 44ትን እንመልከት።</u>

**<<የንስሓ>>** መሠረታዊ አመጣጥና ጥቅሙ በብሉይ ኪዳን በዐጭሩ ሲገለጽ እንደዚህ አሁን እንደሰማነው ሲሆን <u>በሐዲስ ኪዳን ደግሞ</u> በልዩ ልዩ የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍል ተዘግቦ እናገኘዋለን።

## <u>ክፍል 28፥</u>

## <u>ንስሓ በሐዲስ ኪዳን፥</u>

<u>በሐዋርያት ሥራ 3፥14 ጀምሮ፥ በተለይም ከቍጥር 17 ብንመለከት፥</u>

<u>ሐዋርያው</u> ቅዱስ ጴጥሮስ የአይሁድ ሕዝብን ፈጣሪ፣ የዓለም መድኃኒት የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን ያለጥፋት አሳልፋችሁ ለሞት ሰጥታችኋልና፣ የንጹሕ ሰው ደምን በከንቱ አፍሳችኋልና፤ ይቅር እንዲላችሁ፣ ኃጢአታችሁም ይደመሰስ ዘንድ ንስሓ ግቡ በማለት አስተምሯቸዋል። <u>(ግብ ሐዋ) የሐዋ· ሥራ 3፥19።</u>

<u>በሐዋ ሥራ ምዕራፍ 2፥37 ብንመለከትም፥ ሐዋያው</u> ቅዱስ ጴጥሮስ ኃጢአታችሁ ይሰረይ ዘንድ ንስሓ ግቡ ብሎ ካስተማራቸውና ከመከራቸው ሕዝብ መካከል ከሦስት ሺሕ የሚበልጡ ሰዎች ትምህርቱን ተቀብለው በሥራ ላይ እንዳዋሉና ተፀፅተው ከበደላቸው ተመልሰው፣ ንስሓ ገብተው ተጠምቀው እንደዳኑ እንገነዘባለን። <u>(ግብ ሐዋ) የሐዋ ሥራ 2፥37</u>

<u>ቅዱስ ጴጥሮስ ጸጋ እግዚአብሔርን</u> በገንዘብ ለመለወጥ (ለመግዛት) የሞከረውንም ሰው የልብህን ሓሳብ ይቅር ይልህ ዘንድ ስለዚህ ከፋትህ ንስሓ ግባ በማለት መክሮታል። <u>የሐዋ ሥራ 8፥22።</u>





<u>ቅዱስ ጴጥሮስ</u> ካህን ስለ ሆነ የንስሓ ኑዛዜ ሥልጣነ ክህነት ላላቸው አባቶች ካህናት ብቻ የሚነገር ልዩ ምሥጢር እንደሆነ፥ መልሱና አፈጻጸሙም በአባቶች በካህናት ብቻ የሚሰጥ የጥፋት መመለሻ፣ የበደል ሩጫ መግቻ፣ መንፈሳዊ ልጓም፥ የስሕተት ማረሚያ፣ የሕይወት ማስተካከያ መሣሪያ መሆኑንም ከዚሁ መረዳት እንችላለን።

ይህ ከዚህ በላይ የተጠቀሰው እኛ ሰዎች በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ባጠፋነው ጥፋት በበደልነውም በደል ተፀፅተን፣ ነገ ከነገ ወዲያ ሳንል ዛሬ፥ ከአሁኑ ጀምሮ በፍጹም ልባችን ወደ ፈጣሪአችን ወደ እግዚአብሔር ብንመለስ፥ አምላካችን የምሕረትና የይቅርታ አምላክ በመሆኑ ይቅር እንደሚለን ከኃጢአታችን ሁሉ ነጻ አድርጎ መንግሥቱንና ጽድቁን እንደሚያወርሰን የሚያረጋግጥልን ነው።

አዎ ቅዱስ ቃሉ እውነተኛውን ፍቅር መሠረት በማድረግ፥ እየጾምን፣ እየጸለይን በፍጹም ትሕትና ሆነን፣ በንጹሕ ልብ ወደ እርሱ ቀርበን ልንለምነው እንደሚገባንና ሁለተኛም እግዚአብሔርንና ሰውን የሚያሳዝን የኃጢአት ተግባር መፈጸም ተገቢ እንዳልሆነ ነው እየመከረን ያለው።

<u>በተጨማሪም ከዚህ ቀጥለው ያሉትን ቀስ ብለን እንመልከታቸው</u>

<u>1ኛ</u> ነገር ግን <u><<ንስሓ>></u> የሚገቡትን ምክንያት ሰጣቸው፣ ተስፋቸውን ያጡ ሰዎችንም ደስ ያሰኛቸዋልና <u><<በንስሓ>></u> ወደ እግዚአብሔር ተመለስ፥ ኃጢአትንም ተዋት ከኃጢአትህ ተመልሰህ በፊቱ ተለማመጥ፥ ፈጽመህ ከኃጢአትህ <u><<በንስሓ>></u> ወደ እግዚአብሔር ተመለስ፣ ኃጢአትን ሁሉ ጥላ የእግዚአብሔርንም ፈቃድ ፈጽም። <u>ሲራክ 17፥24 ጀምሮ</u>

<u>2ኛ</u> የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር ወደ እኔ <u><ተመለሱ></u> ይላል። <u>ዘካ 1፥3</u> (ንስሓ ግቡ ማለት) ነው።

<u>3ኛ</u> <u>ንስሓ ግቡ</u> ኃጢአትም ዕንቅፋት እንዳይሆንባችሁ ከኃጢአታችሁ ሁሉ ተመለሱ፣ የበደላችሁትን በደል ሁሉ ከእናንተ ጣሉ፣ አዲስ ልብና አዲስ መንፈስም ለእናንተ አድርጉ <u>ሕዝ 18፥30</u>

<u>4ኛ</u> ሰው በችኰላ ለእግዚአብሔር የተቀደሰ ነው ብሎ ቢሳል፥ ከተሳለም በኋላ <u><ቢፀፀት></u> ወጥመድ ነው። <u>መጽሐፈ ምሳሌ 20፥25</u> (ፀፀት ማለት በግእዝ ቋንቋ ንስሓ ነው)

5ኛ በንስሓ ወደ እኔ የተመለሰውን እጠብቀዋለሁ።
መጽሐፈ መቃብያን ሣልስ 7፥4

6ኛ አንተ <በንስሓ> መለማመጥ ተሳነህ፣ ከመሬት የተፈጠረ አዳም ግን ስለ ኃጢአቱ በእግዚአብሔር ፊት ፈጽሞ እያለቀሰ <በንስሓ> ተመለሰ።

ያ አዳም ግን በልቅሶና በኀዘን ወደ ንስሓ ተመለሰ።
መጽሐፈ መቃብ ሣልስ 4፥23,4፥ 26 7፥4 10፥16, 10፥27 እንመልከት።

7ኛ በዚያም ወራት መጥምቁ ዮሐንስ መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና <ንስሓ> ግቡ ብሉ በይሁዳ ምድረ በዳ እየሰበከ መጣ ማቴ 3፥1

8ኛ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ኢየሱስ መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና <ንስሓ> ግቡ እያለ ይሰብክ ጀመር። ማቴ 4፥17

9ኛ ለማንም እንዳትናገር ተጠንቀቅ ነገር ግን ሔደህ ራስህን ለካህን አሳይ። ማቴ 8፥4።

አሳይ ማለት ራስህን በካህን አማካይነት <በንስሓ> አስመርምር፣ ንስሓ ግባ ማለት ሲሆን ቃሉ በደላችንን ለንስሓ አባታችን ብቻ መናገር እንደሚገባን ነው የሚያስረዳን።

10ኛ <ንስሓ> በሚገባ በአንድ ኃጢአተኛ በእግዚአብሔር መላእክት ፊት ደስታ ይሆናል። ሉቃ 15፥10።

11ኛ ሰው ሆይ አንተ ከእግዚአብሔር ፍርድ የምታመልጥ ይመስልሃልን?

ወይስ የእግዚአብሔር ቸርነት ወደ <ንስሓ> እንዲመራህ ሳታውቅ የቸርነቱንና የመቻሉን የትዕግስቱንም ባለጠግነት ትንቃለህን?

ነገር ግን እንደ ጥንካሬህና <ንስሓ> እንደማይገባ (በማይገባ) ልብህ የእግዚአብሔር ቅን ፍርድ በሚገለጥበት በቍጣ ቀን ቍጣን በራስህ ላይ ታከማቻለህ። ሮሜ 2፥3





12 አስቀድመውም ኃጢአትን ከሠሩትና ስለአደረጉት ርኵሰትና ዝሙት መዳራትም <ንስሓ> ካልገቡት ወገን ስለ ብዙዎች ምናልባትም አዝናለሁ ብዬ እፈራለሁ።
2ኛ ቆሮ 12፥21።

13 አሁን <ለንስሓ> ስላዘናችሁ ደስ ብሎኛል እንጂ ስላዘናችሁ አይደለም።

(አሁን ደስ ብሎኛል ደስታዬም ስላዘናችሁ ሳይሆን ኀዘናችሁ ለንስሓ ስላበቃችሁ ነው) 2ኛ ቆሮ 7፥9,
እንዲሁም 2ኛ ጴጥ 2፥18 ጀምሮ እስከ ፍጻሜው።

14 እንግዲህ ከወዴት እንደወደቅህ አስብ <ንስሓም> ግባ፥ የቀደመውንም ሥራህን አድርግ፥ አለዚያ እመጣብሃለሁ <ንስሓም> ባትገባ መቅረዝህን ከሥፍራው እወስዳለሁ። ራዕ ዮሐ 2፥5

መቅረዝ ማለት አንድ እግር ሆኖ ብዙ ቅርንጫፍ ያለው የሻማ ማብሪያ ቀንዲል ነው ራዕ ዮሐ 1፥12, 11፥4 እንመልከት።

15 <<እርስ በርሳችሁ በኃጢአት ተናዘዙ፥ ትፈወሱም ዘንድ እያንዳንዱ ስለ ሌላው ይጸልይ የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይልን ታደርጋለችና ይላል>> ያዕ 5፥16 ጀምሮ፥

16 ሊቀ ካህናት ሁሉ ስለ ኃጢአት መባንና መሥዋዕትን ሊያቀርብ ከሰው ተመርጦ ለእግዚአብሔር በሆነው ነገር ሁሉ ስለ ሰው ይሾማልና ላልተማሩትና ለሚስቱት ሊራሩላቸው ይችላል። ዕብ 5፥1።

(ቃሉ የንስሓ አባት የሚያስፈልግ መሆኑን የሚያመለክት ነው)።

<<ጥቅሶቹ አስፈላጊው ማብራሪያ እየተደረገባቸው ከልዩ ልዩ የአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እንዳሉ የተወሰዱ ናቸው>>

# ምዕራፍ 8፥

## ኀ ሰንበትና የሰንበት መሠረታዊ ምሥጢር፥

**ሰንበት ማለት ምን ማለት ነው?**

**በዐቢይ ጾም ውስጥ የሚገኙ የሰንበታት፥ (የእሑዶች) መሠረታዊ ምሥጢርስ ምንድ ነው?**

ሰንበት ማለትስ ምን ማለት ነው?
ለሚለው ጥያቄ መልሱ ከዚህ ቀጥሎ ይገኛል።

ሰንበት ማለት 7ኛ ማለት ነው።

ሰንበት፥ <<ሰንበተ አከበረ>> ከሚል የግእዝ ግስ ስለሚገኝ የክብር ቀን ማለትም ነው።

ዕለተ ሰንበት ስንልም፥ የክብርና የዕረፍት ቀን ማለታችን ነው።

ይኸውም በኦሪት ዘፍጥረት ከምዕራፍ 1፥1,፥

በዘፀአትም ከምዕራፍ 20፥8 ጀምሮ እንደምንመለከተው፥

እግዚአብሔር በስድስቱ ቀናት ፍጥረቱን ሁሉ ሲፈጥር ሰንብቶ በሰባተኛው ቀን (ቅዳሜ) ዕረፍቱን አደረገ።

በዘፀ ምዕራፍ 20፥1 ጀምሮ ከሚገኙት የጌታችን የሕግና የትእዛዝ ቃላትም አንዱ ሰንበትን አክብሩ የሚል ስለሆነ ሰንበት በእግዚአብሔር የተባረከች፣ የተቀደሰች፥ የዕረፍት፣ የክብርና የምስጋና ቀን ናት ማለት ነው።

በተጨማሪም ዘፍጥ 1፥1, ዘፀ 20፥11።





# ክፍል 29፥

## ቅዳሜ

ቅዳሜ፥ ቀዳሚት ሰንበት እየተባለች ትጠራለች።
ትርጉሙ፥ አንደኛይቱ፣ የመጀመሪያይቱ፣ ጥንታዊቷ ሰንበት (ቅዳሜ) ማለት ሲሆን፥ ከቀዳሚት በፊት ሌላ የተመረጠች የክብር፣ የዕረፍትና የምስጋና የሆነች ዕለተ ሰንበት እንደሌለችና ይህች ቀዳሚት ሰንበት (ቅዳሜ) የመጀመሪያ መሆኗን ነው የሚያስገነዝበን።

ስለዚህ በብሉይ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት በተለያየ ክፍል የሚገኘው ስለ ሰንበት የሚገልፅ ሁሉ ቅዳሜ እየተባለች የምትጠራውን ይህችን ቀዳሚት ሰንበትን የሚመለከት ሆኖ፥ ሰንበተ ክርስቲያንንም በትንቢታዊ ምሥጢር ይጠቊማታል ማለት ነው።

ቀዳሚት ሰንበት፥ ቀዳሚት፣ ቀዳም፥ ቅዳሜ፣ ሰንበተ አይሁድ የሚል መጠሪያ ያላት ስትሆን፥ እኛ ሰንበተ ክርስቲያንን በልዩ ደረጃ እንደምናከብራት ቀዳሚት ሰንበት በአይሁድ ዘንድ ከጥንቱ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ከሌሎች ዕለታት ይልቅ ለየት ባለ መልኩ እንደምትከበር ይታወቃል።

ሊቁ ኢትዮጵያዊ ቅዱስ ያሬድም ሰንበትን በጣዕመ ዜማው አመሥጥሯታል።

በግእዙ ሲጠቀስ፥ <<ሰንበት ተዐቢ እምኵሉ ዕለት ወሰብእ ይከብር እምኵሉ ፍጥረት፥ አዕበያ ኖኅ በውስተ ታቦት፥ አብርሃም አከበራ በውስተ ምሥዋዕ፥ እዝማቹም ይቀጥላል። አዘዞሙ ሙሴ በትእይንት ያክብሩ ሰንበተ በጽድቅ>> ይላል።

የአማርኛ ትርጉሙም፥ ሰንበት ከሁሉ ዕለት ትበልጣለች፣ ሰውም ከሁሉ ፍጥረት ይበልጣል፥ ኖኅ በታቦት (በመርከቡ) ውስጥ ከፍ ከፍ አደረጋት፥ አብርሃምም በመሠዊያው አከበራት፥ ሙሴ ደግሞ ሕዝበ እስራኤል ሰንበትን በአንድነት ሆነው በእውነት እንዲያከብሩዋት አዘዛቸው ማለት ነው።
(ይህ ድጓ ከክረምት መዝሙር የተጠቀሰ ነው)።

እንደዚሁም <<ሰንበትሰ በእንተ ሰብእ ተፈጥረት ወአኮ ሰብእ በእንተ ሰንበት>> ይላል።

ትርጉሙ፥ ሰንበት ስለ ሰው ተፈጥራለች እንጂ ሰው ስለ ሰንበት አልተፈጠረም ማለት ነው። ማር 2፥27።

ይህ ቅዱስ ቃል ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረው ሲሆን፥ ቅዱስ ያሬድም በጣዕመ ዜማው ጠቅሶታል።

ይኸውም ሰንበት ከሁሉም ዕለታት እንደምትበልጥና በአርአያ ሥላሴ የተፈጠረው ሰውም ከሁሉም ፍጥረት የበለጠ፣ የከበረ እንደሆነ ነው የሚያስረዳን።

እኛ ሕዝበ ክርስትያን ቀዳሚት ሰንበትን (ቅዳሜን) መጽሐፋዊ ሥርዓቷንና ታሪካዊ መሠረቷን በመጠበቅ በሐዲስ ኪዳን ተበንቶ በተቀመጠልን የሥርዓተ ሃይማኖት አፈጻጸምና የበዐላት አከባበር መሠረት እናከብራታለን።

## ክፍል 30፥

## ሰንበተ ክርስቲያን (እሑድ)

እሑድ ማለት አንድ ማለት ሲሆን፥ እሑድ ማለቱ ሰንበት የፍጥረት መጀመሪያ ስለሆነች አንደኛ፣ ጥንተ ዕለት፣ (የፍጥረት መጀመሪያ) መሆኗን ሲያመለክተን ነው።

ከላይ በሰፊው እደተገለጸው ዘፍጥረትን 1፥1 መጽ. ኩፋሌንም 2፥1 ጀምሮ እንመልከት።

### ይህች ሁላችንም ፈጣሪያችንን በማመስገን በልዩ ክብር የምናርፍባት አስቀድማ በምሥጢራዊ ትንቢት የተጠቀሰች ሰንበተ ክርስቲያን (የክርስቲያን ሰንበት)

በሐዲስ ኪዳን የተከበረች ሰንበት ስትሆን፥ በጌታችን የተመረጠች መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ድውያንን የፈወሰባት፣ የተነሣባትና ልዩ ልዩ ተአምራቱንም ያደረገባት፥ በክርስቶስ ክርስቲያን ለተባልነው የክብር፣ የዕረፍትና የምስጋና ዕለት እንድትሆነን የመደባት በዓለም ፍጻሜም በእርሷ ቀን መጥቶ ፍጥረቱን ሁሉ የሚያሰናብትባት ዕለት ናት።





### ሰንበተ ክርስቲያን (የክርስቲያን ሰንበት)

ስሟ እንደሚያመለክተን ለእኛ ለሕዝበ ክርስቲያን በፈጣሪአችን በልዩ ክብር የተሰጠችበት ዋናው ዓላማ፥ ዝም ብለን ተቀምጠን እንድንውልባት ሳይሆን፥ መንፈሳውያን ሥራዎችን እንድናከናውንባት

ማለትም እግዚአብሔር አምላካችንን ከሌሎች ዕለታት ይልቅ ለየት ባለ መልኩ እንድናመሰግንባት፥ ስለ ነፍሳችን ዘለዓለማዊ ሕይወት እንድንጸልይባት፥ በሰላምና በእውነተኛ ፍቅር አንድ በመሆን ፈጣሪአችንን በልዩ ልዩ ዝማሬ እያመሰገን የነፍስ ዕረፍት፣ የመንፈስ ደስታ እንድናደርግባት፥

የታመሙትንና የታሠሩትን እንድንጠይቅባት፣ የተጣሉትን እንድናስታርቅባት፥ የተራቡትን እንድንመግብባት፥ (እንድንመጸውት) የተቸገሩትንም ሁሉ በሚቻለን ዐቅም እንድንረዳባት ነው።

ጥቅስ <<እግዚአብሔር አምላክህ እንዳዘዘህ በሰንበት ቀን ትቀድሰው ዘንድ ጠብቅ>> ዘዳ 5፥11

በዕለተ ሰንበት ወደቤተ ክርስቲያን ሑዶ እግዚአብሔርን ማመስገን እንደሚገባ ሲያስገነዝበን ነው።

በዕለተ ሰንበት እግዚአብሔርንና ሰውን ከሚያሳዝን ነገር ሁሉ ተጠብቀን የጽድቅን ሥራ ብቻ እንድንሠራ መታዘዛችንን ሲነግረንም እንደዚህ ይላል።.

<<ሰንበትን የሚያከብር እጁንም ክፋትን ከማድረግ የሚጠብቅ ሰው ብፁዕ ነው>>። ኢሳ 56፥2።

በሰንበት ወደ ጸሎት ቦታ መሔድ እንደሚያስፈልግ ሲያስረዳን ደግሞ <<በሰንበት ቀንም ከከተማው በር ውጭ የጸሎት ሥፍራ በዚያ መሆኑን ስለአሰብን ወደወንዝ አጠገብ ወጣን>> ይላል። ግሐ (የሐዋ ሥራ) 16፥13።

አዎ ሰው ከሁሉ ፍጥረት እንደሚከብር ሰንበትም እግዚአብሔር ስለመረጣት ከሁሉም ዕለታት ትበልጣለችና ከዚህ በላይ በየደረጃው እንደተገለጸው ሥጋዊውን ተግባር ሳይሆን መንፈሳዊውን የጽድቅ ሥራ ብቻ ልንሠራባት ይገባናል ማለት ነው።

## ምዕራፍ 9፥

# በዐቢይ ጾም ውስጥ የሚገኙት ሰንበታት፥

በዐቢይ ጾም ውስጥ የሚገኙት ሰንበታት፥ ደግሞ የተለያየ የመጠሪያ ስም አላቸው።

ይኸውም በየዓመቱ የዐቢይ ጾም መጀመሪያው (መግቢያ) የሚገኘው ሰንበት (እሑድ) << ዘወረደ>> ለዐቢይ ጾም መቅድሙ፥

ወይም መግቢያውና ዋዜማው ነው ማለት ነው።

ስለሆነም የዐቢይ ጾም (የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጾም) መጀመሪያ እሑድና ሳምንቱ << ዘወረደ>> ይባላል።

ከዘወረደ ቀጥሎ ያለው <<ቅድስት>>

ከቅድስት ቀጥሎ ያለው <<ምኲራብ>>

ከምኲራብ ቀጥሎ ያለው <<መፃጕዕ>>

ከመፃጕዕ ቀጥሎ ያለውም <<ደብረ ዘይት>>

ከደብረ ዘይት በኋላም <<ገብር ኄር>>

በመጨረሻው የሚገኘውም <<ኒቆዲሞስ>> በመባል ይታወቃሉ።

ከዚሁ ከኒቆዲሞስ በኋላ፥ <<ሆሳዕና>> በበነገታው ሕማማት ሲሆን፥





በሳምንቱም <<ትንሣኤ ክርስቶስ>> {{ፋሲካ}} ይሆናል ማለት ነው።

እነዚህ <<ሰንበታት>> በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጾም ውስጥ የሚውሉ ሲሆኑ፥ ጌታችን ልዩ ልዩ አምላካዊ ሥራውን የሠራባቸው፥ የድኅነት፣ የተአምራት፣ የምስጋና እና የታሪክ ዕለታት ናቸው።

<<ሰንበታት>> ስማቸው እንደሚጠቍመን ምሥጢራቸውም በስያሜያቸው መሠረት ሰፋ ያለ ይዘት ያለው ነው።

በቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን የምስጋና እና የአገልግሎት ሥርዓት መሠረት በአንድ እሑድ የጀመረ የዕለት ስያሜም (ስምም) እስከሚቀጥለው እሑድ ድረስ ይሰነብታል።

ለምሳሌ፥
የዐቢይ ጾም መግቢያ ዋዜማ እሑድ <<ዘወረደ>> ሲሆን፥

ሰኞም፣

ማክሰኞም፣

ሮብም፣

ሐሙስም፥

ዓርብና ቅዳሜም ከእሑድ እስከሚቀጥለው እሑድ ድረስ ያሉት ቀናት በሙሉ <<ዘወረደ>> ይባላሉ።

ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ <<ቅድስት>> የሚባል እሑድ ሳምንቱን <<ከዘወረደ>> ተቀብሉ እስከ ቀጣዩ እስከ <<ምኲራብ>> ድረስ ይይዘዋል።

ሌሎችም በዚሁ መሠረት ከዓመት እስከ ዓመት ይቀጥላሉ ማለት ነው።

## ክፍል 31፥

## <<ዘወረደ>>

የመጀመሪያ ጾም መግቢያ ሰንበት ዘወረደ እየተባለ መጠራቱ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰማይ ወርዶ ከድንግል ማርያም በመወለዱ ወረደ፣ መጣ፣ በመባሉ፥ ምክንያት እንደሆነና

ጾሙም ጾመ ሕርቃል መባሉ ሕርቃል ለተባለ የሮም (የቢዛንታይን) ገዥ ስለ ተጾመ እንደሆነ ከቦታው በሰፊው ተገልጿል። ገጽ 72ና 73 እንመልከት።

## ክፍል 32፥

## ቅድስት፥

## <<ቅድስት የዐቢይ ጾም 2ኛ እሑድና ሳምንት>>

ይህች እሑድና ሳምንት **<<ቅድስት>>** በመባል የምትታወቅ ስትሆን የዐቢይ ጾሙን ሁለተኛ ሳምንት የምንጀምርባት ወቅት ናት።

**<<ቅድስት ማለት>>** እመቤታችን ከሁሉም ፍጥረት የተለየች ንጽሕትና ቅድስት እንደሆነች ሁል ጊዜ በእመቤታችን ክብርና ቅድስና ክፍል እንደሚገለጸው፥ የቅድስት ዕለትም ከሌሎች ዕለታት ተለይታ በጌታችን ለጾም፣ ለነፍስ መድኃኒት ተመርጣ የተከበረች ቅድስት ዕለትና ሳምንት ናት ማለት ነው።

ቅድስት የምትባለው እለትና ሳምንቷ ጌታችን በመብል ምክንያት የጠፋውን ሕይወታችንን ያለ መብል በጾም ለመመለስ፥

ለሁላችንም አብነቱን ለመስጠት እኛንም በተግባር ለማስተማር ሲል መዋዕለ ጾሙን የጀመረባት፥

በጌታችን፣ በፈጣሪኣችን ለፍጹም ሕይወት የተመረጠች፣ የተቀደሰች ናት።





ስለሆነም ከዚህ ቀጥለን የቅድስት እሑድ ቃለ እግዚአብሔርን መሠረት በማድረግ ሁሉንም በየክፍላቸውና፣ በየደረጃቸው እንመለከታቸዋለን።

የቅድስት እሑድ የቅዳሴው ምስባክ በግእዙ ሲጠቀስ፥

እግዚአብሔርሰ ሰማያተ ገብረ፥
አሚን ወሠናይት ቅድሜሁ፥
ቅድሳት ወዕበየ ስብሐት ውስተ መቅደሱ፥ ይላል።
መዝ 95፥5።

ይህ መዝሙር፥ ልበ አምላክ የተባለው ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት እግዚአብሔር አምላክ ነውና ሰባቱን ሰማያት ፈጠረ፥ ምስጋና፣ ቅድስነትና ግርማ በመቅደሱ ውስጥ ናቸው፣ ሃይማኖትና ምግባርን የያዘ ሰውንም ይወዳል።

<<ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ>> ተብሎ መመስገን ዐቢየ ስብሐት መባል ገንዘቡ ነው።

(ምስጋና የባሕርዩ ነው) በማለት ፈጣሪውን አመስግኖበታል።
<<በአበው ትርጓሜ መሠረት ሲብራራ>>

የፍጥረታት ባለቤት የሆነው ፈጣሪያችን ልዑል እግዚአብሔር ሰባቱን ሰማያትንና በሰማያት ያሉትን ፍጥረታት ሁሉ ፈጠረ፥ ዓለምንና በውስጧ ያሉትንም ሁሉ ፈጠረ ሃይማኖትና ቅድስና የእርሱ ነው፥ ምስጋና የባሕርዩ ቢሆንም በኦሪት ዘፍጥረት 1፥26 ጀምሮ እንደምንመለከተው ሰውና መላእክት በእርሱ አርአያና አምሳል የተፈጠሩበት ዋና ዓላማም እርሱን ለማመስገን እንደመሆኑ መጠን ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ተብሎ መመስገን የሚገባው ነውና ፍጥረትን ሁሉ ካለመኖር ወደ መኖር አምጥቶ ለፈጠረ ለእግዚአብሔር አምላካችን በሰማያትም በምድርም ምስጋና ይድረሰው።

ከዚህ በላይ እንደተገለጸልን እግዚአብሔር ሃይማኖትን ከምግባር ጋር አጣምሮ የያዘውን፣ ሃይማኖቱን በመልካም ምግባር፣ በሠናይ ሥራ የሚገልጸውን ሰው ይወዳል፥ ይረደዋል የሃይማኖት ትርጉም መልካም ምግባር ነውና፥ መገለጫውም በጎው ሥራ ስለሆነ አንድ ሰው ሃይማኖት አለው ሊባል የሚቻለው የሃይማኖት ሥራ ሲሠራ የታየ እንደሆነ ነው።

ይኸውም፥ እውነተኛ ፍቅር፥ ንጽሕና፥ ትሕትና፥ ጾም፥ ጸሎት፥ ርኅራኄና ምጽዋት፤ በአጠቃላይ እግዚአብሔርንና ሰውን የሚያስደስት መልካም ምግባር፥ ሠናይ ሥራ ነው።

በተለይም የዚህ ሁሉ የጽድቅ ሥራ ማሠሪያው እውነተኛው ፍቅር በመሆኑ እውነተኛው ፍቅርን መሠረት አድርገን ከዚህ በላይ የተጠቀሰውን መልካሙን ሥራ ሁሉ መሥራት ይገባናል ማለት ነው።

ነቢዩ ዳዊት በመዝሙሩ የዘመረው የቅድስት ምስባክ ውስጠ ምሥጢሩ በአበው ትርጓሜ መሠረት ሲተነተን እንደዚህ አሁን እንደሰማነው ነው።

ቅዱስ ወንጌሉ ደግሞ፥ <<ወሶበ ትጸውሙ ኢትኩኑ ከመ መደልዋን>> ይላል፥ ማቴ 6፥16 ነው።

ስትጾሙም እንደ ግብዞች አትጠውልጉ፥ ሰነፎች ጾመኞች እንደሆኑ ሰው ያውቅላቸው ዘንድ ፊታቸውን አጠውልገው፥ ግንባራቸውን ቋጥረው፥ ሰውነታቸውንም ለውጠው ይታያሉና እንደነዚህ አትሁኑ። እናንተስ በምትጾሙበት ጊዜ ራሳችሁን ተቀቡ፥ ፊታችሁንም ታጠቡ፤ ጾመኞች መሆናችሁን ሁሉን የሚያውቅ አባታችሁ ጌታ እንጂ ሌላሰው አይወቅባችሁ። በማለት ጌታችን አስተምሮናል።

የዚህ ምሥጢራዊ ትንታኔ ስትጾሙ በስውር ይሁን ያለው፥

በጾመ ፈቃድ ማለትም በግል ለትሩፋት በምትጾሙበት ጊዜ ማለቱ ነው እንጂ በቤተ ክርስቲያናችን በሥርዓተ ቀኖና የተመደበውን፥ በግልጽ በኅብረት የምንጾመውን የዓዋጁን ጾም ማለቱ አይደለም።

ምክንያቱም በቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓተ ቀኖና የተወሰነ ጾም እማ በመንፈሳዊ ሕግ የተደነገገ፥ በመጽሐፋዊ መመሪያ የታዘዘ፤ በግልጽ፤ በይፋ የሚታወጅ ስለሆነ የዓዋጅ ጾም ነው የሚባለው።

በሰባቱ አጽዋማት ውስጥ ያለ ጾም፥
የማኅሌቱ፥ የሰዓታቱ፥ የስብሐተ ነግሁ፥ የቅዳሴውና የጸሎተ ሠርኩ፥ በአጠቃላይ የጾሙና የጸሎቱ ጊዜያት በቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓተ ቀኖና ስለ ተወሰነ በውሳኔው መሠረት ነው በኅብረት ሆነን በግልጽ የምንጾመው።



<<ቅድስት>> የዐቢይ ጾም 2ኛ እሑድና ሳምንት >>

ራሳችሁን ተቀቡ ማለቱ ደግሞ እውነተኛውን ፍቅር ያዙ እርስበእርሳችሁ ተፋቀሩ ሲለን ነው።

ፊታችሁን ታጠቡ ማለቱም፥ ንጽሕናንና ትሕትናን ገንዘብ አድርጉ፤ በትሕትና፤ በንጽሕና ሆናችሁ ጹሙ፤ ጸልዩ፤ እያለቀሳችሁ ንስሓ ግቡ ሲለን ነው።
<<በአበው ትርጓሜ መሠረት ሲብራራ ነው>>

በመሆኑም የዚህ ምሥጢር ተራራ ተብሎ በሚጠራው አንቀጸ <<ብፁዓን የጌታችን ትምህርት፥ ብፁዓን እለ ይርህቡ ወይፀምዑ በእንተ ጽድቅ ብሎ >> ተብራርቶ እናገኘዋለን።

ይኸውም፥ አብዝተን ከተመገብን፥ አብዝተን ከጠጣን እማ ሰውነታችንን ወስነን ገተን ማኖር እንዴት ይቻለናል ብለው የሚበሉትንና የሚጠጡትን ቆጥበው የሚራቡ ንዑዳን ክቡራን ናቸው።

ጨርሰን ከተመገብን፥ ጨርሰን ከጠጣን እማ መንግሥተ ሰማያትንስ በምን እንዋጃታለን ብለው ከሚበሉት ከሚጠጡት ከፍለው ለነዳያን ሰጥተው (መጽውተው) የሚራቡ የሚጠሙ (የሚጾሙም) ንዑዳን ክቡራን ናቸው።

እንዲሁም ከመብልዓ ኃጢኣት፥ ከስቴ ኃጢአት የሚራቡ፥ ማለትም ኃጢኣትን ከማድረግ፥ የኃጢኣትን ተግባር ከመፈጸም፥ እግዚአብሔርንና ሰውን የሚያሳዝንን ሥራ ከመሥራት የሚቆጠቡ ንዑዳን ክቡራን ናቸው።

በመማር፥ በማስተማር፥ በምናኔ በንስሓ የሚራቡ ንዑዳን ክቡራን ናቸው። በመንግሥተ ሰማያት ይጠግባሉና፥ ማለትም መንግሥተ ሰማያት የተዘጋጀችው ይህን ለሚፈጽሙ ሰዎች ስለሆነች መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ናት። ብሎአል ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ።

አዎ ይህን መልካሙን ሥራ ሠርተው የተገኙ ሰዎች መንግሥተ ሰማያት እንደሚወርሱ የመንግሥተ ሰማያት ባለቤት የሆነው ፈጣሪአችን በማይለወጥ ቃሉ አረጋግጧል።
ማቴ 5፥6

እንግዲህ የጾም ትክክለኛ ተግባር ይህ ነውና ቃሉን በሥራ መተርጐም የእኛ ክርስቲያናዊ ግዴታ ነው ማለት ነው።

ከዚህ በላይ ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው ቅድስት፥ የዐቢይ ጾሙን ሁለተኛ ሳምንት የምንጀምርባት ስትሆን፥

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ለመጾም መዋዕለ ጾሙን የጀመረባት ዕለትና ሳምንት በመሆኗ የጌታችን ጾም መጀመሪያና መታሰቢያ ናት ማለት ነው።

ጌታችን በተለያዩ ሦስት የስሕተትና የኃጢአት ጎዳናዎች፥ ማለትም በስስት፣ በትዕቢትና በአፍቅሮ ርእስ (ራስ ወዳድነት) ይኸውም ሥጋዊውን ሹመት በመሾም፣ ግላዊ ዝናን፣ ግላዊ ክብርንና ገንዘብን መውደድ ማለት ነው።

በነዚህ የኃጢአት ርእሶች በሚባሉት የመጣውን ሰይጣን፥ በአንፃራቸው ተሰልፎ፥ በጾም፣ በትዕግሥትና በትሕትና ድል አድርጎ ጾም የሥጋና የነፍስ ፍጹም መድኃኒት መሆኑን በተግባር አሳይቶ ለራሱ ጹሞ እኛንም ጹሙ ብሎናል።

በጾም፥ በጸሎት የተለያዩትን ፈተናዎች ማለፍ፥ ሰይጣንንና ሰይጣናዊ ጠላትን ማሸነፍ እንደሚቻልም በተግባር አስተምሮናል። ማቴ፥ 4፥1።

ሐዋርያት፥ አርድእትና ሊቃውንትም እርሱን አብነት በማድረግ ጹመዋል በጾም በጸሎት ድውያንን ፈውሰዋል፣ ሙታንንም አስነሥተዋል፣ ብዙ ተአምራትን አድርገዋል።

እኛ ደግሞ ጌታችንን፥ ሐዋርያትን፣ ቅዱሳንና ሊቃውንት አባቶቻችንን አብነት አድርገን ልንጾም፣ ልንጸልይ፣ በእነርሱ እግር ልንተካ ይገባናል።

ከቅዱስ መጽሐፉ እንደምንረዳው ጌታችን ጾሙን ገዳመ ቆሮንቶስ (ወደ ቆሮንቶስ በረኻ) ገብቶ እንደቆመ ሳይቀመጥ፣

ሰውነቱን ሁሉ እንደዘረጋ ሳያጥፍ፣ አንዳችንም ዕረፍት ሳያደርግ፥ አርብዓ መዓልትና አርብዓ ሌሊት (አርባ ቀንና አርባ ሌሊት) በሚጾምበት ጊዜ፥ ከዚህ በላይ በተጠቀሱት የስሕተትና የጥፋት ጎዳናዎች ለማሰናከል የመጣውን ሰይጣን ድል ካደረገ በኋላ መላእክት ሊያገለግሉት ቀርበው እንደ ነበር። ቅዱስ ወንጌሉ ያስረዳናል። ማቴ 4፥11





እኛም ትምህርቱንና ተግባራዊ አብነቱን በመቀበል ጾሙን በአግባቡ ከጾምነው መላእክት ይረዱናል፣ መንፈስ ኃይል፣ መንፈስ ረድኤት ይሰጠናል፣ ስርየተ ኃጢአትን እናገኛለን።

ሰማያዊ ክብርንም ከጌታችን መድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ እንቀዳጃለን ማለት ነው።

በተጨማሪም ከዚህ በታች ያሉትን ጥቅሶች እንመልከታቸው፥

1ኛ በጾማችሁ ቀን ፈቃዳችሁን ታደርጋላችሁ፣ ሠራተኞቻችሁን ሁሉ ታስጨንቃላችሁ፣ ለጥልና ለክርክር ትጾማላችሁ፣ በግፍ ጡጫም ትማታላችሁ፣....እኔ የመረጥኩት ጾም ይህ ነውን?....

በውኑ ይህን ጾም በእግዚአብሔር ዘንድ የተወደደ ቀን ትለዋለህን? ኢሳ 58።3።

(ይህ ቅዱስ ቃል ጾማችን እውነተኛ እንዲሆን ነው በመገሠጽ እየመከረን ያለው)።

2ኛ እግዚአብሔርን አመስግኑ ስሙንም ጥሩ ተቀኙለት ዘምሩለት ሥራውን ሁሉ ለአሕዛብ ንገሩ። መዝ 104፥1

3ኛ ክብርንና ምስጋናን ለእግዚአብሔር አምጡ በቅድስናውም ሥፍራ ለእግዚአብሔር ስገዱ። መዝ 28፥2

4ኛ የልቡናችሁን ወገብ ታጥቃችሁና በመጠን ኑራችሁ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲገለጥ የምታገኙትን ጸጋ ፈጽማችሁ ተስፋ አድርጉ። 1ኛ ጴጥ 1፥13።

ይህ ቅዱስ ቃል ሁል ጊዜ በሚመስገንበት፣ ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙም በሚፈተትበት በቤተ ክርስቲያኑ፣ (በቤተ መቅደሱ) እየተገኘን እግዚአብሔር አምላካችንን ማመስገን እንደሚገባን ነው እየነገረን ያለው።

<<ጥቅሶቹ ለአስፈላጊው ማብራሪያ እየተደረገበት እንዳሉ ከአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የተወሰዱ ናቸው>>።

# ክፍል 33

## ምኩራብ የዐቢይ ጾም 3ኛ እሑድ፥

ምኩራብ ማለት፥ በቀጥታ ሲተረጐም አዳራሽ ማለት ሲሆን፥ ጌታችን ወደ አይሁድ ቤተ ጸሎት፣ ምኩራብ (አዳራሽ) ገብቶ ቤቴ የጸሎት ቤት እንጂ የንግድ ቤት አይደለም በማለት ያስተማረበት በቤተ ጸሎቱ ውስጥ ሲነግዱ፣ ሲሸጡ፣ ሲለውጡ የነበሩትን ሰዎች ያስወገደበት መታሰቢያ ነው።

ጌታችን ወደ አይሁድ ምኩራብ (የአይሁድ አዳራሽ) ወይም ቤተ ጸሎት በገባ ጊዜ የመማማሪያ፥ የጸሎት ቤትና የሥርዓተ አምልኮ ማስፈጸሚያ የሆነውን ምኩራብ አይሁድ መገበያያ፣ መሸጫና መለወጫ አድርገውት ስለ አገኛቸው ቤቴ የጸሎት ቤት ይባላል።

እናንተ ግን መገበያያ መሸጫና መለወጫ አደረጋችሁት በማለት ሸቃጮች ሰዎቹንና እንስሳቱን በጅራፍ እየገረፈ ሰዱቃቸውንም (መደረደሪያቸውንም,ገበታዎቻቸውንም) እየገለባበጠ አባርሮአቸዋል።

የሃይማኖት ትምህርቱንም እዚሁ ምኩራብ ውስጥ ገብቶ አስተምሮአል።

አዎ ጌታችን ቤተ ክርስቲያን (ቤተ መቅደስ) የእግዚአብሔር መመስገኛ፣ የምሕረትና የይቅርታ መለመኛ፣ የነፍስ ገበያ፥ የሕይወት ማግኛ እንጂ፥ የሥጋ ገበያ፣ የግለ ሰቦች መጠቃቀሚያ ልትሆን እንደማይገባት በምኩራብ አይሁድ ተገኝቶ አረጋግጧል።

ትምህርቱን፣ ምክሩንና መመሪያውንም ሰጥቷል።

አዎ ምሥጢራዊ መልእክቱ ሁላችንንም ስለሚመለከት ልብ ብለን ልንገነዘበው፥ ልናስተውለውም ይገባናል።

ስለዚህም ይህ የዐቢይ ጾም ሦስተኛ እሑድና ሳምንቱ ከዚህ በላይ በተጠቀሰው ምሥጢር ምክንያት ምኩራብ እየተባለ ይጠራል ማለት ነው። ዮሐ 2፥13።

በተጨማሪም ከዚህ በታች ያሉትን ጥቅሶች እንመልከት።

1ኛ የቤትህ ቅንዓት በልታኛለችና፣ የሚሰድቡህም ስድብ





በላዬ ወድቆአልና፣ ነፍሴን በጾም አስመረርኋት። መዝ 68፥9

(ጥቅሱ ከምኩራብ ምስባክ የተወሰደ ነው)።

2ኛ እንጀራህን ለተራበ ትቆርስ ዘንድ ስደተኞችን (ድኾችን) ወደ ቤትህ ታገባ ዘንድ የተራቆተውንስ ታለብሰው ዘንድ፣ ከሥጋ ዘመድህ እንዳትሸሸግ አይደለምን?

የዚያን ጊዜ ብርሃንህ እንደ ንጋት ይበራልሃል፣ ፈውስህም ፈጥኖ ይበቅላል፣ ጽድቅህም በፊትህ ይሔዳል፥ የእግዚአብሔርም ክብር በኋላህ ሆኖ ይጠብቅሃል። ኢሳ 58፥7

3ኛ ፍጹም ልትሆን ብትወድ ሒድና ያለህን ሁሉ ሸጠህ ለድኾች ስጥ፣ መዝገብም በሰማያት ታገኛለህ፥

መጥተህም ተከተለኝ። ማቴ 19፥21

ቅዱስ ቃሉ ምጽዋት በእግዚአብሔር ዘንድ ትልቅ ዋጋን እንደሚያሰጥ ነው የሚያስረዳን።

በተጨማሪም ማቴ 12፥7 ሆሴዕ 6፥6 2ኛ ቆሮ 9፥7 ገላ 13፥16 ዳን 4፥27 ማር 4፥24 ሉቃ 7፥47 እንመልከት።

4ኛ ምጽዋትን የሚመጸውት ሰው ለእግዚአብሔር በማደሩ ነው። መጽሐፈ ሲራክ 29፥1

5ኛ ወንድሞቼ ሆይ እምነት አለኝ የሚል ሥራ ግን የሌለው ሰው ቢኖር ምን ይጠቅመዋል?

እምነቱስ ሊያድነው ይችላል? ያዕቆብ 2፥14።

ይህ ቅዱስ ቃል መልካም ሥራ (ምጽዋት)የሌለው እምነት ብቻ እንደማይጠቅም ነው እያስገነዘበን ያለው

<<ጥቅሶቹ ለአስፈላጊው ማብራሪያ እየተደረገበት እንዳሉ ከአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ የተወሰዱ ናቸው>>።

## ክፍል 34፥

## መፃጉዕ የዐቢይ ጾም 4ኛ እሑድ፥

መፃጉዕ ማለት በሽተኛ ማለት ሲሆን፥ በዮሐንስ ወንጌል 5፥5 ጀምሮ እንደምናገኘው ጌታችን ለ38 ዓመታት ያህል በደዌ ዳኛ በአልጋ ቍራኛ ተይዞ፥ (በጽኑዕ በሽታ ታሞ) ሲማቅቅ የነበረውን መፃጉዕ በመባል የሚታወቀውን በሽተኛ ሰው የፈወሰበት መታሰቢያ ነው።

ይህ መፃጉዕ በመባል የሚታወቀው በሽተኛ ለ38 ዓመታት ያህል በጽኑዕ ደዌ ተይዞ ታሞ እያለ ተስፋን ባለመቍረጥ ለመዳን ደጅ ሲጠናበት በነበረው ሥፍራ ሕሙማን ፈጥነው ገብተው እየተጠመቁ ከደዌያቸው የሚፈወሱበት ውሃ ነበር።

ይኸውም የእግዚአብሔር መልአክ በሳምንት አንድ ጊዜ መጥቶ ውሃውን ሲባርከው ውሃው ስለሚንቀሳቀስ የውሃውን እንቅስቃሴ ሰምቶ ቀድሞ የገባ አንድ በሽተኛ ተጠምቆ ሲወጣ ከደዌው ሁሉ ይፈወስ እንደነበርና መፃጉዕም በውሃው ተጠምቆ ከደዌው መዳን ይፈልግ ነበር።

ነገር ግን መፃጉዕ ቀድሞ ለመግባት ዐቅም ስለአልነበረው፤ ተሸክሞ ከመጠመቂያው የሚያኖረውም ሆነ የሚያጠምቀው ወገን ስለሌለው ይህን ዕድል ማግኘት እንዳልቻለ ቅዱስ መጽሐፋችን ይናገራል።

ስለሆነም የርኅራኄና የፍጹም ሕይወት አምላክ እግዚአብሔር የበሽተኛውን ልመና፣ ጸሎቱን፣ ገዓሩንና ጭኾቱን ሰምቶ በአንድ ጊዜ ከደዌው ፈውሶ በል ተነሥና አልጋህን ተሸከመህ ወደ ቤትህ ሒድ አለው።

ለ38 ዓመታት ያህል በደዌ ዳኛ በአልጋ ቍራኛ ተይዞ (በጽኑዕ በሽታ ታሞ) ሲማቅቅ የነበረው መፃጉዕም ጌታችን ስለፈወሰው ፍጹም ጤነኛ ሆኖ ታሞ ተኝቶበት የነበረውን አልጋ በመሸከም እየተደነቀ ወደ ቤቱ እንደ ሔደ ይታወቃል።





(መፃጉዕ ለ38 ዓመታት ያህል ተሸክሞት የነበረውን አልጋ እርሱ ደግሞ ድኖ በተራው ተሸከመው)

ይህ እኛም በትክክለኛ እምነታችን ጸንተን ፈጣሪአችን እግዚአብሔርን በንጹሕ ልብ ከለመነው ከደዌ ሥጋ፣ ከደዌ ነፍስ ልያድነን እንደሚችል ነው የሚያስገነዝበን። ዮሐ ወንግጌል 5፥5።

በተጨማሪም ከዚህ በታች ያለውን እንመልከተው፥

እግዚአብሔር በሽተኛውን በደዌው አልጋ ላይ ሳለ ይረዳዋል፣ ከደዌው ፈውሶም መኝታውን ይለውጥለታል።

አቤቱ እኔ ግን ለዚህ የሚያበቃ ሥራ የለኝምና ማረኝ ይቅርም በለኝ፣ አንተን በድያለሁና ነፍሴን ፈውሳት ይላል ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት በመዝሙሩ። (መዝ 40፥3)

አዎ ይህ ቅዱስ ቃል ከዕለቱ ምስባክ የተጠቀሰ ሲሆን፥ በፍጹም ልባችን ወደ እግዚአብሔር አምላካችን ከቀረብን፣ ፈጣሪያችንን በንጹሕ ልብ ከለመን፥ ከእርሱ ፍጹም ምሕረትና ፍጹም ሕይወት እንደሚገኝ ነው እያመለከተን ያለው።

## ክፍል 35፥

## ደብረ ዘይት የዐቢይ ጾም 5ኛ እሑድ

<<ደብረ ዘይት>> የዐቢይ ጾም 5ኛ እሑድ ነው።

ዘይት የወይራ ስም ሲሆን፥ ደብርም ተራራ ማለት ነው።

ስለዚህም <<ደብረ ዘይት>> ማለት የወይራ ዛፍ ያለበት ተራራ ማለት ነው።

<<ደብረ ዘይት>> በምሥራቃዊ ኢየሩሳሌም በቀድሞ የሰሎሞን ቤተ መቅደስ ትይዩ የሚገኝ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱ ሐዋርያትን ሰብስቦ የዳግማይ ምጽአቱንና የዓለም ፍጻሜ ሁኔታን በምሳሌ አድርጎ ያስተማረበት ተራራ ነው።

<u><<ደብረ ዘይት>> ከኢየሩሳሌም በስተምሥራቅ 75 ኪ.ሜ ርቀት ላይ እንደሚገኝ ይታወቃል።</u>

<u>(1 ኪ.ሜ ያህል, የሰንበት መንገድ ያህልም ይላል የሐ, ሥራ 1÷12)</u>

በዐቢይ ጾም ውስጥ ያለው የጾሙ <u>5ኛ</u> እሑድና ሳምንቱም <<ደብረ ዘይት>> ይባላል።

<<ደብረ ዘይት>> በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 24÷1 ጀምሮ እንደምንመለከተው የጌታችን ዳግማይ ምጽአትንና የዓለም ፍጻሜ ሁኔታን የምናስታውስበት ዕለት ነው።

ጌታችን የሚመጣበት ዓመተ ምሕረትና ሰዓቱ ተለይቶ ባይታወቅም÷ ዘመኑ ዘመነ ዮሐንስ፣ ወሩ ወርኀ መጋቢት፣ ዕለቱ ዕለተ እሑድ፣ ጊዜውም መንፈቀ ሌሊት እንደሚሆን በአባቶቻችን ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ተገልጾአል።

ነገር ግን ብዙ ዘመነ ዮሐንስ፣ ብዙ ወርኀ መጋቢት፣ ብዙ ዕለተ እሑድና ብዙ መንፈቀ ሌሊት ስለ አለ÷ በዚህ ጊዜ ነው ተብሎ ሰዓቱ ተለይቶ እንደማይታወቅ የተነገረ ሲሆን÷ የመቃረቡ ምልክቶችና ምሳሌዎቹ ደግሞ ከላይ በተጠቀሰው <u>የማቴዎስ ወንጌል 24÷1</u> አማካይነት በጌታችን አንድ ባንድ ስለ ተገለጹ ልብ ብለን ልናስተውላቸው ይገባናል።

ጌታችን ምንም እንኳን የሚመጣበት ጊዜ ባይታወቅም መምጣቱ ግን አንዳችም ጥርጥር ስለሌለው ሰው ሁሉ በሃማኖትና በሃይማኖታዊ መልካም ምግባር ዝግጁ ሆኖ እንዲኖር አስቀድሞ መክሮአል፣ እንዳትሳሳቱ ብሎም አስጠንቅቆአል።

<u>ጌታችን ደቀ መዛሙርቱ ሐዋርያትን ደብረ ዘይት</u> በተባለው ቦታ ሰብስቦ ከእኔ በኋላ በስሜ የሚነግዱ ብዙ አታላዮች ይመጣሉና እንዳትታለሉ ማንም እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ ሁል ጊዜም ዝግጁዎች ሆናችሁ ኑሩ በማለት አስተምሮአቸዋል። ትምህርቱና መልእክቱ ሁላችንንም ይመለከታል።

<u>አዎ በመዝሙር 49÷2 ጀምሮ</u>÷ <<እግዚአብሔርሰ ገሀደ ይመጽእ፣ ወአምላክነሂ ኢያረምም፣ እሳት ይነድድ ቅድሜሁ>> ተብሎ በግእዙ እንደተጠቀሰልን እግዚአብሔር አምላካችን በግልጽ ይመጣል፣ መጥቶም ዝም አይልም በጻድቃንና በኃጥአን መካከል ሆኖ ይፈርዳል። ለሁሉም እንደየሥራው ይሰጠዋል። ለጻድቃን ይፈርድላቸዋል በኃጢአተኞች ላይም ይፈርዳል ማለት ነው።





በሚመጣበት ጊዜ እሳት በፊቱ ይቃጠላል በዙሪያውም ብዙ ዐውሎ አለ ይላል ነቢዩ ዳዊት።

ይህ ማለት ጻድቃን የሚድኑበት ሕይወት፣ ኃጥአን ግን የሚጠፉበት መቅሰፍት በባሕርዩ አለ ማለት ነው።
<u><<በአበው ትርጓሜ መሠረት ሲብራራ ነው>></u>

አዎ በቅዱሳት መጻሕፍት+ በተለይም ደግሞ <u>በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 24+1</u> ጀምሮ ተዘርዝሮ እንደሚገኘው እግዚአብሔር አምላካችን በማይታወቅ ጊዜና ባልተጠረጠረ ሰዓት በግርማ መንግሥቱ በድንገት መጥቶ ጻድቃንን ኑ ወደ እኔ ብሎ ይጠራል፣ ለጻድቃን ጽድቅን መንግሥተ ሰማያትን ያወርሳል።

ኃጥአንን ግን ወግዱ ከእኔ ራቁ ለሰይጣንና ለመልእክተኞቹ ወደ ተዘጋጀው፣ እሳቱ ለዘለዓለም ወደማይጠፋው ሒዱ ብሎ ያሰናብታል፣ ለኃጥአን ገሃነመ እሳትን ፈርዶ ይሰጣል።

ሰማይንና ምድርን÷ ሌላውንም የፈጠረውን ፍጥረት ሁሉ ከሀልዎ፣ ከምንት+ (ከመኖር) ወደ ኢሀልዎ፣ ወደ ኢምንት÷ (ወደ አለመኖር) ያሳልፋል፣ ፍጥረቱን ሁሉ ያሰናብታል። እርሱ ግን ኅልፈት የሌለበት ዘለዓለማዊ የሆነ የባሕርይ አምላክ ነው።

ስለዚህ ጌታችን አስቀድሞ ያችን የማታዳግመውን የከባድ ፍርድ ቀን መጨረሻ አታውቁትምና ሁል ጊዜ ተዘጋጅታችሁ ኑሩ ብሎ ነግሮናል።

ኦርቶድክሳዊት ተዋሕዶ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንም ይህን የጌታችን ቃል መሠረት አድርጋ÷ በእምነታችን እንድንጸና፣ ሃይማኖታችንን በመልካም ምግባር እንድንገልጽ÷ ሕጉንና መመሪያውን እንድንጠብቅ፣ ትእዛዛቱን እንድንፈጽም፣

የተቸገሩትንም ባለን ዐቅም እንድንረዳ፣ በሰላምና በእውነተኛው ፍቅር አንድ ሆነን÷ እየጾምን፣ እየጸለይን፣ በፀንብዓ ንስሓ እየታጠብን፣ (ንስሓ እየገባን)ማለትም ኃጢአታችንን እየተናዘዝን÷ እግዚአብሔርንና ሰውን ከሚያሳዝን ማንኛውም የኃጢአት ተግባር ተቆጥበን ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን እየተቀበልን ድንገተኛ የሆነውን የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ምጽአት ዝግጁዎች ሆነን እንድንጠባበቅ በመምህራንና በአባቶች ካህናት አማካይነት ዘወትር ታስተምረናለች፣ አሁንም እያስተማረችን፣ እየመከረችን ትገኛለች።

አዎ ትምህርቱ ሁል ጊዜ ይሰጣል እንሰማዋለን ነገር ግን መስማት ብቻ እንደማያጸድቅ በቅዱስ መጽሐፋችን ተነግሮናልና በሰማነው መሠረት መልካሙን ሥራ መሥራት ይጠበቅብናል። ያዕ 1፥22 እንመልከት።

ምሥጢረ መጻሕፍትን ከሊቃውንት አባቶቻችን ተምረን፥ ስለ እምነታችን፣ ስለ ሃይማኖታችንና ስለ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን መንፈሳዊ ሥርዓት ከመሠረቱ በማወቅ እምነታችንን በሠናይ ሥራ መግለጽ፣ ሃይማኖታችንን በመልካም ምግባር ማሳወቅ አለብን።

ምክንያቱም እምነት የሥራ መሠረት እንደመሆኑ መጠን፥ መልካም ምግባርም የእምነት መታወቂያና ራስ ነው።

ስለዚህ ሃይማኖት ሊታወቅ የሚችለው በመልካም ምግባር ሲገለጽ ነው።

በመሆኑም ነው ሃይማኖት ያለ ምግባር ምግባርም ያለ ሃይማኖት ምንም እንደማይጠቅም በቅዱስ መጽሐፋችን የተነገረን። ያዕ 2፥14 እንመልከት።

አንድ ሰው ሃይማኖት አለው ሊባል የሚችለው የሃይማኖትን ሥራ ሲሠራ የታየ እንደሆነ ነው ብለናል።

መልካም ምግባር ሠናይ ሥራ ማለትም ጾም ጸሎት ምጽዋት፣ ርኅራኄ፣ ትሕትና እና እውነተኛው ፍቅር ሲሆን በተለይም እውነተኛው ፍቅር የእነዚህ መልካም ሥራዎች ሁሉ ዋና ማሠሪያ እንደሆነም ተደጋግሞ ተገልጿል።

ይኸውም እውነተኛው ፍቅር ካለ ሌሎችም የጽድቅ ሥራዎች ሁሉ በእውነተኛው ፍቅር ውስጥ ሊካተቱ ስለሚችሉ ነው።

አንድ ሰው ወንድሙን በእውነት የሚወደው ከሆነ ችግር ቢደርስበት ያዝንለታል ይራራለታል ይጠይቀዋል በሁሉም ዐቅሙ ይረዳዋል። ይህ ማለት ደግሞ መጸወተ፣ የታመመውንና የታሠረውን ጠየቀ፣ ለተቸገረው ራራ። በአጠቃላይ በቅዱስ ወንጌል ማቴዎስ 25፥34 የሚገኘውን <<ተርቤ አብልታችሁኛልና ተጠምቼ አጠጥታችሁኛልና፣ እንግዳ ሆኜ ተቀብላችሁኛልና፣ ታርዤ አልብሳችሁኛልና፣ ታምሜ ጠይቃችሁኛልና፣ ታሥሬ ወደ እኔ መጥታችሁ ጠይቃችሁኛልና የተባረካችሁ ናችሁ ኑ ወደ እኔ>> የሚለውን የጌታችንን ቃል ፈጸመ ማለት ነው።





የምንጾመው ጾም ትርጉም ያለው ጾም ሊሆን ይገባዋል። የጾም ምሥጢርና ተግባራዊ ትርጉም ለሁላችን ግልጽ እንዲሆንልን ያስፈልጋል።

አዎ የጾም ትርጉም፥ ትሕትና፣ ይቅር ባይነት፣ የዋህነትና ደግነት ነው።

የጾም ተግባራዊ ትርጉም፥ ርኅራኄና ምጽዋት ነው። የጾም ዋና ማሠሪያው እውነተኛ ፍቅር ነው።

የምንጾመው ጾም ትርጉም ሊኖረው የሚችለው ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን እግዚአብሔርንና ሰውን የሚያስደስቱ መልካሞች ሥራዎችን የሠራን፣ ሕገ እግዚአብሔርን ያከበርን፣ መመሪያውን የጠበቅን፣ ትእዛዙንም የፈጸምን እንደሆን ነው። ከዚህ ውጭ የምንጾመው ጾም ግን ለታይታ፣ ለይምሰል የምናደርገው ትርጉም የሌለው ጾም ሊሆንብን ነው ማለት ነው።

በተለይም ደግሞ ምጽዋት ከመሥዋዕት እንደሚበልጥና በእውነተኛው ፍቅርም ሌሎች የኃጢአት ተግባራት ሊሸፈኑ (ሊደመሰሱ) እንደሚችሉ በቅዱስ መጽሐፍ ተደጋግሞ ተነግሮናልና እነዚህን ገንዘብ ማድረግ ተገቢያችን ነው። 1ኛ ጴጥ 4፥8።

ይቅር ባይነት፥ ይልቁንም ወንድምን ልክ እንደራስ አድርጎ ማየት፣ በእውነተኛው ፍቅር መውደድ ከዋናው ትእዛዝ 2ኛው ነው። ዘሌዋ 19፥18 ማቴ 22፥39።

አዎ አባታችን ሆይ እያልን ሁል ጊዜ የምንጸልያት በማቴዎስ ወንጌል ምዕ 6፥9 የምትገኝ የዘወትር ጸሎታችንም በውስጧ በቅዱሳት መጻሕፍት የሚገኙ 5 ዐበይት መንፈሳውያን ቁም ነገሮች እንዳሏት ይታወቃል።

እነርሱም፥ 1ኛ ሃይማኖት፥ 2ኛተስፋ፥ 3ኛ ፍቅር፥ 4ኛ ትሕትና እና 5ኛ ጸሎት ናቸው።

1ኛ ሃይማኖት፥ ያላዩትን እንዳዩት አድርገው አቅርበው አባታችን ሆይ በሰማይ የምትኖር እያሉ መጸለይ፣

2ኛ ተስፋ፥ መንግሥትህ ትምጣ እያሉ መንግሥተ ሰማያትን የሕይወት ተስፋ አድርገው መጠባበቅ፣

<u>3ኛ ፍቅር፥</u> ለእኔ ብቻ ሳይሉ በደላችንን ይቅር በለን በማለት አንዱ ስለ ሌላው መጸለይ ስለ ወንድሙ መራራት መተዛዘን፥ ይኸውም፥ በደላችንን ይቅር በለን ማለት ስለሌላውም መጸለይ ነው በደሌን ይቅር በለኝ ቢል ኑሮ ግን ለራሱ ብቻ መጸለይ ማለት ስለ ሆነ ራስ ወዳድ ይሆን ነበር።

<u>4ኛ ትሕትና፥</u> እያንዳንዱ ኃጢአታችንን (በደላችንን) ይቅር በለን እያለ መጸለዩ፣ ኃጥእም ቢሆን ጻድቅ፥ ኃጢአተኛ ነኝ በማለት በትሕትና ሆኖ በደላችንን ይቅር በለን እያለ ይጸልያል።

<u>5ኛ</u> አምስተኛውም ጸሎት ነው።

ይህች ታላቅ ጸሎት ከዚህ በላይ እንደተገለጸው ልዩ የሆነ መንፈሳዊ ጥቅምና ብዙ ምሥጢርም ስለአላት ሁል ጊዜ ብንጸልያት መልካም ነው።

ታዲያ ግን እኛም የበደሉንን ይቅር እንደምንል (እንድንል) የሚለው በውስጧ የሚገኘውን ጽኑዕ ውል በየጊዜው እያጸናነው መሆናችንን በመረዳት ከፈጣሪአችን ጋር የምንዋዋለውን ውል በተግባር መፈጸም አለብን።

ማንንም ማስቀየም የለብንም፣ የበደሉንንም ሁሉ ይቅር ልንል ይገባናል።

ይህ ካልሆነ ግን በፈጣሪአችን ላይ እየቀለድን፥ አሊያም ራሳችንን ባራሳችን እያታለልን ነን ማለት ነው።

<u>ምክንያቱም በዚሁ ምዕራፍ ከቍጥር 14 ጀምሮ ማለትም ማቴ 6፥14።</u> ለሰዎች ኃጢአታቸውን ይቅር ባትሉ ኃጢአታችሁ አይቀርላችሁም ተብለናል።

ይኸውም ምንም ሳንበድላቸው የበደሉንን በክፉ ተግባራቸው ያስቀየሙንን ነው እንጂ ወዳጆቻችንንማ ስለሚወዱን እንወዳቸዋለን ስለሚረዱንም እንረዳቸዋለን ይህ ብድር ነው።

በዓለማችን ሲታይ ከነፍሰ ገዳይ የከፋ ጠላት እንደሌለ ለሁላችንም ግልጽ ይመስለኛል።

ይኸውም ጌታችን የሰደቡት በክፉ ተግባራቸው ያሳዘኑት፥ የገረፉት፣ የቸነከሩትና የሰቀሉት፣ ሞትን የፈረዱበት እንዲማሩ፥ በዕኩይ ተግባራቸው ተፀፅተው፣ ከክፉ ሥራቸውም ተመልሰው፣





ንስሓ ገብተው እንዲጸድቁ፣ የእርሱ ወገኖች እንዲሆኑ ነው አባት ሆይ ይህን ማድረጋቸው ባያውቁ ነውና እኔ የባሕርይ አምላካቸውና ፍጹም መድኃኒታቸው መሆኔን ተረድተው ወደ እኔ እንዲመጡ አድርጋቸው፥ ማራቸው፣ ይቅርም በላቸው በማለት በመስቀል ላይ ሆኖ ወደ ባሕርይ አባቱ ወደ እግዚአብሔር አብ የጸለየው። እግዚአብሔር ጠላቶቹን እዚያው በአንድ ጊዜ ማጥፋት ይችል ነበር ነገር ግን አላጠፋቸውም።

ምክንያቱም እግዚአብሔር የርኅራኄና የይቅርታ አምላክ ስለ ሆነ የፈጠራቸው ሁሉ እንዲማሩ፣ በእኩይ ተግባራቸው ተፀፅተው፥ ከክፉ ሥራቸው ተመልሰው ንስሓ ገብተው እንዲጸድቁ የእርሱ ወገኖች እንዲሆኑ እንጂ እንዲጠፉ አይፈልግም።

<<እኛስ? እኮ እኛስ ምንድ ነው የምናደርገው?
ጥያቄው እያንዳንዳችንን የሚመለከት ሲሆን፥
ተግባራዊ መልሱም ከእያንዳዳችን ይጠበቃል>>

አዎ እኛም በክፉ ተግባራቸው የሚያስቀይሙንንም ልባቸው በጎ ሐሳብ፣ እጃቸውም ወደ መልካም ሥራ እንዲመለስ እየጸለይን ከልባችን ይቅር ልንላቸው፣ በእውነትም ልንወዳቸው ይገባናል ማለት ነው።

ስመ ክርስትናን በመቀበል ክርስቲያን የተባልነው በክርስቶስ ስለ ሆነ የክርስቶስን መልካም ምግባር መሥራት፣ የእርሱን ሠናይ አርአያ እየተከተልን ወገኖቻችንን በእውነተኛው ፍቅር ልንወድ፣ ልንረዳቸውም ተገቢያችን ነው።

ጌታችን በዮሐንስ ወንጌል እኔ እንደወደድኋችሁ እርስበርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ ትእዛዜ ይህች ናት፥ እኔ ያዘዝኋችሁን ሁሉ ብታደርጉ እናንተ ወዳጆቼ ናችሁ ብሎአልና ቅዱስ ቃሉን ተቀብለን በተግባር ላይ ልናውለው ይገባናል። <u>ዮሐ 15፥12።</u>

ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስም ወንድሙን የማይወድ ነፍሰ ገዳይ እንደሆነና በሞት <u>ውስጥም እንደሚኖር በ1ኛ መልእክቱ በምዕራፍ 3፥14 ጀምሮ ሲያስጠነቅቀን፥</u> ወንድሙን እንደ ራሱ አድርጎ የሚወድና በእውነተኛው ፍቅር የሚኖር ግን በእግዚአብሔር እንደሚኖርና እግዚአብሔርም ከእርሱ ጋር እንደሆነ በዚሁ መልእክት <u>በምዕራፍ 4፥16 ገልጾልናል</u>።

ይኸውም የጽድቅ ሥራዎች ዋና ማሠሪያ እውነተኛው ፍቅር እንደሆነ ነው የሚያስረዳን ሁሉም መልካም ሥራ ቢሠራ

በእውነተኛው ፍቅር ካልታሠረ ይበተናል ያለ ፍቅር የሚሠራ ሥራ ሁሉ ዋጋ የለውም ማለት ነው።

ለዚህም ነው ቅዱስ ጳውሎስ በሰውና በመላእክት አንደበት ብናገር፣ ትንቢት ቢኖረኝ፣ ሁሉንም ምሥጢር ባውቅ፣ ተራሮችን እስከፈርስ ድረስ እምነት ቢኖረኝ፣ ሥጋዬንም በእሳት እስከሚቃጠል አሳልፌ ብሰጥ ፍቅር ግን ከሌለኝ ምንም አይጠቅመኝም በማለት የተናገረ። 1ኛ ቆሮ ምዕ 13፥1።

እውነተኛውን ፍቅርና ርኅራኄን መሠረት በማድረግ በትሕትና ሆነው እየጾሙ እየጸለዩ እየመጸወቱ ፈጣሪአቸው እግዚአብሔርን የሚማፀኑ ሰዎች ምንኛ የታደሉ ናቸው።

ምክንያቱም ከዚህ በላይ በሰፊው እንደተገለጸው ጌታችን ተራራ ተብሎ በሚታወቀው የማተዎስ ወንጌል ምዕራፍ 5፥6 አንቀጸ ብፁዓን ትምህርቱ+ በማይለወጥ ቅዱስ ቃሉ ተናግሮአል።

ለዚህ የታደልን ስንቶቻችን ነን?

እንጃ በዘመናችን ሌላ ገጽታ ነው እየተከሠተ ያለው፥ በዘመናችን እውነተኛው ፍቅር ርኅራኄ መተዛዘን መረዳዳት የሚባል ነገር ስለ ሌለ ዓለሙ ሁሉ እየተበላሸ፣ እየተጨነቀ ነው የሚገኘው።

ማን ያውቃል በማቴ ወንጌል ምዕራፍ 24፥1 ጀምሮ እንደተነገረን ምናልባትም የጌታችን መምጫ እየተዳረሰ፣ የዓለም መጨረሻ እየተቃረበ ሊሆን ይችላል።

ምክንያቱም ጌታችን ምልክት እንዲሆኑ በምሳሌ አድርጎ የተናገራቸው በዘመናችን እየተፈጸመ ያለውን ሁሉ አንድ በአንድ ያመለክታሉ።

ልብ ብለን ብናስተውላቸው ሁኔታዎቹን ይጠቁማሉ።

<u>ለምሳሌ+</u>

<u>ፍቅር ትቀዘቅዛለች ብሏል፥</u> ከጊዜያዊ ጥቅም፥ ከዓመፅ፣ ከውሸትና ከአልባሌታ የተነሣ እውነተኛይቱ ፍቅር ከእኛ እየጠፋች ናት+ ተንኮል ቅንዓትና ምቀኝነት+ በተለይም ሐሜት፣ ቂምና በቀል በመካከላችን ነግሦአል አብዛኛው ሰው ከአንገቱ በላይ ነው በውሸት ፍቅር ሰላም ሰላም የሚባባለው ዞር ሲል ግን በሓሜት ይተናነካል።





ይህ ደግሞ ማታለያ ነው እንጂ እውነተኛው የእግዚአብሔር ፍቅር አይደለም።

<u>በእኔ ስም ስለምታስተምሩ፣ እኔን ስለምትከተሉ ትናቃላችሁ፣ ትጠላላችሁ ብሏል።</u>

የተነገረው ለጊዜው ለሐዋርያት ቢሆንም ፍጻሜው ግን በሐዋርያት እግር የሚተኩትን፣ የሐዋርያትን ሥራ የሚሠሩ ሁሉንም <u>የክርስቶስ</u> አገልጋዮች ሊቃውንትንና አባቶች ካህናትንም ይመለከታል።

በመሆኑም አባቶችን፣ የቅድስት ቤተ ክርስቲያን እውነተኞች ሊቃውንትንና አገልጋዮች ካህናትን የሚንቁ፥ የተለያየ የማጥላላት ክፉ ስምንም እያወጡ፣ እያዋረዱ የሚያባርሩ፣ የሚያሳድዱ <<ገበርተ እከይ>> ማለትም ክፉ አድራጊዎች፥ ነቃን፣ ሰለጠን ባዮች የሰይጣን መልእክተኞች እየተበራከቱ ናቸው።

<u>እርስ በርስ መጠላላት አሳልፎም ለሞት መሰጣጣት ይኖራል ብሏል፥</u>

ይህውና በዘመናችን ወገን ወገኑን ለጊዜያዊ ጥቅም ሲል ለሞት አሳልፎ ይሰጣል። በመካከላችን ፍጹም የሆነ መተማመን የለም ወገን ወገኑን ይጠረጥራዋል። ደግ፣ ታጋሽና ትሑት ሆኖ መልካሙን ሥራ ቢሠራለትም እንኳ ለምን ይሆን? በማለት በሌላ መንገድ ይመለከተዋል+ እንደ አላዋቂ በመቍጠርም ይንቀዋል እንጂ አያከብረውም፣ በበለጠ አያቀርበውም፣ አይወደውም፣ ከልቡ ሙሉ በሙሉ አያምነውም።

ዓለም ሁሉ የኅሪጥ ነው የሚተያየው፤ ኃይለኛ ነኝ የሚል ደካማውን ለማጥቃት፣ አንዱ ሌላውን ለመጫንና ጨርሶም ለማጥፋት ይጥራል፤ ከቻለ መላውን ዓለም የበላይ ሆኖ ለመቆጣጠር ይሯሯጣል።

ስለ ሥጋዊ ጥቅም ሲል ሥጋውንና ነፍሱን ለሞት አሳልፎ የሚሰጥ ብዙ ነው። ስለ ነፍሱ የሚጨነቅ ግን በጣም ጥቂት ነው።

የአብዛኞቻችን ጸሎት ሥጋዊ ሀብትንና ምድራዊ ብልጽግናን፥ እንዲሁም ለሥጋችን ሙሉ ጤናን ስጠን የሚል ነው እንጂ በነፍሳችን ማረን ኃጢአታችንንና በደላችንን ሁሉ ይቅር ብለህ ለመንግሥተ ሰማያት አብቃን የሚል አይደለም።

ይህ ደግሞ የአረማውያን እንጂ የሕዝበ ክርስቲያን ጸሎት እንዳልሆነ ራሱ ጌታችን ነግሮናል። <u>ማቴ 6፥31</u>

<u>ብዞች ሃይማኖታቸውን ይለውጣሉ ብሏል፥</u>

ሳይማሩ የሚያስተምሩ፣ በክፋትና በተንኮል የሚመራመሩ፣ ተምረው ሳያውቁ ዕድሜ ልካቸው በመደበኛ ጉባኤ የኖሩትን መምህራን በአፈ ጮሌነት እያናናቁ የሚያሰቅቁ፥ መሠረታዊ ዕውቀትና ልባዊ ትሕትና የሌላቸው አወቅን ባዮች ብልጣ ብልጦች በተለያየ ዘዴ ቀስ በቀስ ሃይማኖታችንንና ጥንታዊ ሥርዓቱን ይሸራርፋሉ።

ኦያሌ ወገኖቻችን ትክክለኛው እምነታቸውን በጊዜያዊ ጥቅም እየለወጡ በተለያየ ሁኔታ እየተታለሉ፣ መልካም ምግባራቸውን እየተው፥ ማንነታቸውን በሚገባ የሚያስረዳቸው የራሳቸውን ቋንቋ እየተው፣ መንፈሳዊ ባህላቸውንና ሀገራዊ ታሪካቸውንም እየረሱ፣ በሌሎች ቋንቋና ባህል እየተማረኩ ወደ ጊዜያዊና ወቅታዊ እምነት እየጉረፉ ናቸው።

ስለዚህ፥ ጌታችን አስቀድሜ ተናግሬለሁና ምልክቶቹንና ምሳሌዎቹን ተመልከቱ፣ ሁኔታዎቹን አስተውሉ፣ ማንም እንዳይስታችሁ ተጠንቀቁ። መከራውን ታግሦ ፈተናውን ያለፈ ዘለዓለማዊውን ደስታ ያገኛልና መከራውን ቻሉ፣ ታገሡ በማለት እንዳስገነዘበን፥ በነፍሳችን ዘለዓለማዊውን ሕይወት ለማግኘት በሥጋችን ጊዜያዊን መከራ መቻል፣ ችግሩን መታገሥ፣ ፈተናውንም ሁሉ ማለፍ፥ በእምነታችን መጽናት፣ ሃይማኖታችንንና መንፈሳዊ ሥርዓቱን ሁሉ መጠበቅ፣ ማስጠበቅ ይገባናል ማለት ነው።

አንድ አንድ የጽድቅ ሥራዎችን የሠራን እንደሆን ትልቁን ቁም ነገር ሠርተን የበቃን መስሎን በቂ ነው በማለት እንኩራራ ይሆናል። መልካሙን ሥራ መሥራታችን ጥሩ ነው። ነገር ግን እንጨምርበት ምክንያቱም የእግዚአብሔር መንግሥት (መንግሥተ ሰማይ) በብዙ ድካም እንጂ በቀላሉ፣ በዋዛ ፈዛዛ እንደማትገኝ በቅዱስ መጽሐፋችን ተደጋግሞ ተገልጾልናል። <u>የሐዋ ሥራ 14፥22</u>

ጌታችን ለእኛ ሲል የተቀበለው መከራም ብዙ ነው ምንም ተወዳዳሪ የለውም።

ለዚህ የቅዱስ መጽሐፋችን አንድ ምሳሌን መጥቀስ ይቻላል፥

ይኼውም፥





አንድ አባ ጳኩሚስ የተባለ መናኝ ባሕታዊ አባት እየጸለየ ፈጣሪውን እየለመነ በብዙ ድካም ሲሰግድ ላቡ መሬትን አራሰውና እግዚአብሔር ድካሙን አይቶ ስለተገለጸለት፣ አባ ጳኩሚስ እፎዬ አንተን ፈጣሪዬን አገኛለሁ ብዬ ይኸውና እንደዚህ እደክማለሁ እንዳለውና ጌታችን ደግሞ እኔም እንጂ ለአንተ ብዬ እንደዚህ ሆኜ ተሰቅያለሁ ብሎ በዕለተ ዓርብ እንደ ተሰቀለ ሆኖ እንደታየው የቅዱስ መጽሐፋችን የትርጓሜው ታሪክ ያስረዳናል።

<u><<ከአባቶች ትርጓሜ የተጠቀሰ ነው>></u>

<u>አዎ ጌታችን</u> ለእኛ ሲል የተቀበለው መከራ በማንም በምን ሊለካ አይችልም፣ <u>ሲመጣም</u> ለባሕታዊው አባት እንደታየው በዕለተ ዓርብ እንደተሰቀለ ሆኖ (መስሎ) ነው ለወቀሳ የሚመጣ ስለሚባል በዚህ ጊዜ ማን ከፊቱ ቆሞ ጥያቄውን እንደሚመልስ እንጃ?

ለጥያቄው ትክክለኛውን መልስ ለመስጠት ከአሁኑ በመልካም ምግባር መዘጋጀት ይገባል ማለት ነው።

<u>ጌታችን በማቴዎስ ወንጌል</u> እንዳስጠነቀቀን የሚመጣበት ሰዓት አይታወቅምና፣ እኛ ራሳችን ከዚህ ካለንበት ጊዜያዊ ስፍራ በሞት የምንጠራበትን ጊዜ አናውቅምና ኃጢአታችንን እየተናዘዝን ከማንኛውም የነውርና የኃጢአት ተግባር በመታቀብ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙንም እየተቀበልን ለመንግሥተ ሰማይ ዝግጁዎች ሆነን መኖር ተገቢያችን ነው። <u>ማቴ 24፥36</u>

አዎ ሁል ጊዜ እንደሚነገረን፥ አሁንም በእየደረጃው እንደተገለጸልን እውነተኛውን ሃይማኖታችንን ከመልካም ምግባር ጋር ይዘን የጽድቅን ሥራ ሳንሠራ ሞት የቀደመን እንደሆነ በፈጣሪአችን ፊት ቆመን በምንጠየቅበት ጊዜ ፍጹም ሕይወትን የምናገኝበት አጥጋቢ መልስ ሊኖረን ስለ ማይችል የጽድቅ ሥራ፣ መልካም ምግባር የሚባለው ጾም፣ ጸሎት፣ ርኅራኄ፣ ምጽዋት፣ ትሕትና እና እውነተኛው ፍቅር ሁል ጊዜ በመካከላችን እንዲኖር ያስፈልጋል።

የጽድቅና የርኅራኄ ባለቤት የሆነው ፈጣሪያችን ልዑል እግዚአብሔር ኃጢአታችንንና በደላችንን ሁሉ ይቅር ብሎ በሚመጣበት ጊዜ በቀኙ አቁሞ፥

<<የተባረካችሁ ናችሁና ኑ ወደ እኔ>> በማለት

የማያልፈውን ጽድቁን መንግሥተ ሰማያትን እንዲያወርሰን፥ በእምነታችን ጸንተን፣ እውነተኛውን ፍቅር መሠረት አድርገን፣

በመልካም ምግባር ታንጸን፣ ሕጉን ጠብቀን፣ መመሪያውንም አክብረን፣ ትእዛዛቱን እየፈጸምን፣ እየጾምን፣ እየጸለይን፣ የተቸገሩትን ወገኖቻችን ሁሉ ባለን ዐቅም እየረዳን መኖር ይገባናል።

ኃጢአታችንን እየተናዘዝን፥ ከማንኛውም ነውርና አሳዛኝ ተግባር ንጹሓን በመሆንም፣ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን እየተቀበልን፣ መንግሥተ ሰማያት ለመውረስ፥ የጽድቅና የመንግሥተ ሰማያት ባለቤት የሆነው ሁሉም የሚቻለውን ፈጣሪአችን እግዚአብሔርን ከልባችን እያለቀስን መለመን ያስፈልገናል ማለት ነው።

በተጨማሪም ከዚህ በታች ያሉትን እናስተውላቸው፥

1ኛ በቀልና ፍርድ የእኔ ነው። ዘዳግ 32፥35

ይህን ስናስተውለው እንደየሥራችን ይፈረድልናል (ይፈረድብናል) ማለት ነው።

2ኛ የወደደኝን እወደዋለሁ፣ ያከበረኝንም አከብረዋለሁ።

በንስሓ ወደ እኔ የተመለሰውን እጠብቀዋለሁ። መጽ.መቃ. ሣልስ 7፥4

3ኛ ዕውቀት ሳለህ ንስሓ የምትገባበት ይህ ዓለምም ሳለህ አልተዘጋጀህምና የማይረባ ፀፀት ይሆንብሃል።

ገንዘብም ሳለህ የተራበውን አላጕረስኸውምና። መጽ.መቃ. ሣልስ 10፥16

4ኛ በዚህ ዓለም ንስሓን ካልገባን በገሃነም የማይረባ፣ የማይጠቅም ጭኸትንና ልቅሶን እናዘጋጃለን። መጽ.መቃ. ሣልስ 10፥27

5ኛ እንዲህ አይደለም በዚህ ዓለም እንደሠራኸው ሥራ መጠን በጎም ቢሆን፣ ክፉም ቢሆን ተነሥተህ ፍዳህን ትቀበላለህ እንጂ የምትቀር አይምሰልህ።

መጽ. መቃ. ሣልስ 10፥10 ጀምሮ በሰፊው እንመልከተው።





6ኛ ለእግዚአብሔር ብሎ መከራውን ለሚታገሥ ሰው ጠላቱን ተበቅሎ ያጠፋለታል።

ኃጢአቱንም ያስተሰርይለታል። መጽሐፈ ሲራክ 28፥1

7ኛ ነገረ ሠሪ እንደበት ብዙ ሰዎችን አወካቸው፣

ከአንዱ ወገንም ወደ አንዱ ወገን እንዲሰደዱ አደረጋቸው። መጽ. ሲራክ28፥14

8ኛ የሰው ልጅ (ጌታችን) ከመላእክቱ ጋር በአባቱ ክብር ይመጣ ዘንድ አለው ያን ጊዜም ለሁሉ እንደሥራው ያስረክበዋል ማቴ 16፥27

ሁሉም እንደ እየሥራው ዋጋውን ይቀበላል ማለት ነው።

9ኛ በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም። ማቴ 7፥20

10ኛ እንግዲህ ሊመጣ ካለው ከዚህ ሁሉ ለማምለጥ በሰው ልጅም ፊት ለመቆም እንድትችሉ ስትጸልዩ ሁሉ ጊዜ ትጉ። ሉቃ 21፥36።

11ኛ እነሆ በቶሎ እመጣለሁ ለእያንዳንዱም እንደሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ።

አልፋና ኦሜጋ፣ ፊተኛውና ኋለኛው፣ መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ። ራዕ ዮሐ 22፥12

ይህ ቅዱስ ቃል አሁን በሁሉም መዘጋጀት እንደሚገባን ነው አስቀድሞ እያስገነዘበንና እያስጠነቀቀን ያለው።

ኢሳ 51፥6, ማር 13፥33, ሉቃስ 12፥39,1ኛ ተሰ 4፥13, 2ኛ ጴጥ 3፥7፥ ቀስ ብለን እንመልከታቸው።

ጥቅሶቹ ለአስፈላጊው ማብራሪያ እየተደረገበት እንዳሉ ከአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ የተወሰዱ ናቸው።

# ክፍል 36፥

## <<ገብር ኄር የዐቢይ ጾም 6ኛ እሑድ>>

ገብር ኄር የዐቢይ ጾም 6ኛ እሑድ ሲሆን፥ ገብር ኄር ማለት ደገኛ ባሪያ፣ ታማኝ፣ አገልጋይ፣ ቅን፣ ታዛዥ ማለት ነው።

ገብር ኄር ወጥተው ወርደው እንዲያተርፉበት በጌታቸው ገንዘብ በተሰጣቸው ሰዎች ምሳሌ ትምህርት የተሰጠበት መታሰቢያ ነው።

ስለሆነም የዐቢይ ጾም 6ኛ እሑድ ሳምንቱም በዚሁ ምክንያት ገብር ኄር በመባል ይታወቃል፣ ገብር ኄር እየተባለም ይጠራል ማለት ነው። ማቴ 25፥14።

ጌታችን በዘመነ ሥጋዌው በየቦታው እየተዘዋወረ በሚያስተምርበት ጊዜ በልዩ ልዩ ምሳሌ እየመሰለ ሲያስተምር እንደነበር ከቅዱሳት መጻሕፍትና ከሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን አባቶቻችን እንረዳለን።

በመሆኑም በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 24፥1 ጀምሮ እንደተገለጸው ጌታችን የእርሱ መምጣትንና የዓለም ፍጻሜን ለደቀ መዛሙርቱ ለሐዋርያት በኢየሩሳሌም አጠገብ በሚገኘው ደብረ ዘይት በተባለው ቦታ በምሳሌ አድርጎ ካስረዳቸው በኋላ አያይዞም በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 25፥1 ጀምሮ እንደምንመለከተው መንግሥተ ሰማያት ሙሽራን ለመቀበል መብራት ይዘው የወጡትን አሥሩን ቆነጃጅት ትመስላለች በማለት ትምህርቱን ቀጥሏል።

ይኸውም አምስቱ ጠባባት (ልባሞች) ጠንቃቆች ሲሆኑ፥ አምስቱ ግን አብዳት (ሰነፎች) ናቸው ተብለዋል።

ምክንያቱም ልባሞች የተባሉ አምስቱ ዘይቱንም መብራቱንም ሁሉ በጥንቃቄ አዘጋጅተው የሙሽራውን መምጣት ሲጠባበቁ፣ እነዚያ ሰነፎች የተባሉ አምስቱ ግን መብራቱን ቢይዙም ማብራት የሚችሉበትን ዘይት አልያዙም ነበር።

በመሆኑም በዚህ ጊዜ ሙሽራው በድንገት መጣ ሁሉንም አሟልተው ይዘው ተዘጋጅተው ሲጠባበቁት የነበሩት እነዚህ





አምስት ልባሞች በሰዓታቸው ተገኝተዋልና ሙሽራውን በደስታ ተቀበሉት አብረውትም ወደ ሰርግ ሥፍራ በክብር ገቡ ከእርሱ ጋርም ሆኑ።

አምስቱ ሰነፎች ግን በቂ ዘይት ስለአልነበረባቸው ማብራት አልቻሉም። ልባሞችን እባካችሁ ዘይትን አበድሩን ቢልዋቸውም ለእኛና ለእናንተ አይበቃም አይሆንም ከፈለጋችሁ ከሚሸጡት ገዛታችሁ ኑ ስለ አልዋቸው ዘይትን ለመግዛት እንደሔዱ በኋላቸው ሙሽራው ገብቷልና በሙሽራው አቀባበል አልተገኙም።

ሙሽራው ሳያዩት ገባ በሩም ተዘጋባቸው ሰዓት ስለ አለፈ መግባት አልቻሉም ማለት ነው።

ይህ ምሳሌ ነው፥

በትርጓሜው መሠረት ሲብራራ ደግሞ፥ አምስቱ አብዳት (ሰነፎች) የሚላቸው ሃይማኖትን፣ ጾምን፣ ጸሎትን፣ ትሕትናንና ርኅራኄን ይዘው የዚህ ሁሉ ማሠሪያ የሆነውን በቅብዕ ወይም በዘይት የሚመሰለውን ዋናውን እውነተኛውን ፍቅር ያልያዙ ናቸው።

አምስቱ ጠባባት ወይም ልባሞች የሚባሉ ግን፥ ሃይማኖትን፣ ጾምን፣ ጸሎትን፣ ትሕትናንና ርኅራኄን የያዙ ሲሆኑ፥ ከዚህም ጋር የመልካም ምግባር ዋና ማሠሪያ የሆነውን በቅብዕ ወይም በዘይት የሚመሰለውን እውነተኛውን ፍቅር የተጐናፀፉ (የያዙ) ናቸው።

አብዳት (ሰነፎች) ነገ ከነገ ወዲያ እናሟላለን ሲሉ ነበር።

ይኸውም ኃጢአታችንን በሚቀጥለው ጊዜ እንናዘዛለን ቀስ ብለን ንስሓ እንጋባለን በሚቀጥለው ዓመት እንቆርባለን እያሉ ሲኖሩ ባላሰቡት ጊዜ ሞት በድንገት መጥቶ ይወስዳቸዋልና በኃጥአን ሥፍራ ይቀመጣሉ ማለት ነው።

አምስቱ ጠባባት ወይም ልባሞች የተባሉት ግን ሁሉንም አሟልተዋል።

አም ጠባባት (ልባሞች) በሃይማኖት በጾም በጸሎት በትሕትና እና በርኅራኄ ተመሥርተው፥ የዚህ ሁሉ ዋና ማሠሪያ የሆነውን በቅብዕ ወይም በዘይት የሚመሰለውን እውነተኛውን ፍቅር የያዙ፥ ኃጢአታቸውን እየተናዘዙ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን

እየተቀበሉ በሁሉም እየተዘጋጁ ስለኖሩ በጻድቃን ሥፍራ ይቀመጣሉ ማለት ነው።

ሙሽራው በመንፈቀ ሌሊት መጣ ብሏል።
በሙሽራ የሚመሰል ጌታችን ነው ልደቱ ጥምቀቱ ትንሣኤውና ምጽአቱ በመንፈቀ ሌሊት እንደሆነ በሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንና በቅዱስ መጽሐፍ ተነግሯል።

አምስቱ አብዳት ወይም ሰነፎች ልባሞችን ዘይት አበድሩን ቢሉዋቸው አይሆንም ለሁላችንም አይበቃም በማለት መለሱላቸው።

አዎ ሕገ እግዚአብሔር፣ ትእዛዘ መጻሕፍት ለሁሉም በዕኩል በአንድ ዓይነት ነው የታደለው። ትምህርቱና ምክሩ በቤተ ክርስቲያናችን ለመጣው ሕዝበ ክርስቲያን ያለ አድልዎ በአንድነት ነው የሚሰጠውና ሁሉም በተማረው፣ በትእዛዘ ቅዱሳት መጻሕፍት መሠረት በየራሱ መልካሙን ሥራ ሠርቶ እንዲጸድቅ ያስፈልጋል ማለት ነው።

ይኸውም በአንዱ ሥራ አንዱ እንደማይጠቀም፣ በአንዱ ኃጢኣትም አንዱ እንደማይጎዳ የሚያስገነዝብ ሲሆን፥ እያንዳንዳችን በእግዚአብሔር አንድነትና ሦስትነት የማመናችንን፣ በክርስቶስ ክርስቲያን የመባላችንን፣ በቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ አምላኳነት፣ በእግዚአብሔር ወዳጆች ቅዱሳን ጻድቃንና ሰማዕታት በረከትና ረድኤት የመማፀናችንን ምሥጢር በሚገባ መረዳት፣ በእውነተኛው እምነታችን መፅናት፣ ትክክለኛውን ሃይማኖታችንን ከዚህ በላይ በተደጋጋሚ እንደተጠቀሰው በመልካም ምግባር በእውነተኛው ፍቅር መግለጽ እንዳለብን ነው የሚያስገነዝበን።

አዎ ጽድቅና ኩነኔ በእጃችን ስለሆነ የሚያስኩንን ተግባር ከፈጸምን እንኩነናለን የሚያጸድቅ የጽድቅን ሥራ ከሠራን ደግሞ እንጸድቃለን ማለት ነው።

ከዚሁ እንደምንረዳው ልባሞቹ ሰነፎችን ሒዱና ከሚሸጡ ገዝታችሁ ኑ ማለታቸውም ከሥላሴ ምሕረትንና ይቅርታን የሚያሰጡ ነዳያን ስለ ሆኑ ለእነርሱ መጽውቱ ሲሉዋቸው ነው። ምጽዋት ትልቅ ዋጋ እንዳለው ጌታችንም ነግሮናል።
<u>ማቴ. 10፥40, ማር. 9፥37</u>
<u><<በአበው ትርጓሜ መሠረት ሲብራራ ነው>></u>
ነገር ግን ሰነፎች ዕድሉን ሳይጠቀሙበት ነገ ከነገ ወዲያ ሲሉ፥ ጾሙን፣ ጸሎቱን፣ ለትምክሕት፣ ለታይታና ለውዳሴ ከንቱ ብቻ





ይዘውት በእውነተኛው ፍቅር ሳይዘጋጁ ሞት በድንገት መጥቶ ይወስዳቸዋል፤ ሥፍራቸው በሲኦል፥ በመጨረሻም በገሃነመ እሳት ይሆናል።

አምስቱ ጠባባት ወይም ልባሞች የተባሉ ግን ሁሉንም ከእውነተኛው ፍቅር ጋር ስለያዙ መኖሪያቸው ገነት፥ በኋላም መንግሥተ ሰማያት ይሆናል ማለት ነው።

<u>ዋናው መልእክቱ</u> ሁላችንም የጌታችን ምጽአትና የዓለም መጨረሻ ሳይደርስብን፣ እንግዳው ሞት ሳይቀድመን በሁሉም መዘጋጀት እንዳለብን ነው እየመከረን ያለው።

እንደዚሁም ደግሞ ሃይማኖትን ከመልካም ምግባር፣ ንጽሐ ሥጋን ከንጽሐ ነፍስ ጋር ይዘን ሳንመካ እየጾምን፣ እየጸለይን፣ እየመጸወትን፣ በትሕትና በርኅራኄና በትዕግሥት በእውነተኛውም ፍቅር አንድ ሆነን እየተረዳዳን፥ ኃጢኣታችንን እየተናዘዝን፥ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙንም እየተቀበልን ከኖርን ሙሉውን ዝግጅት ማድረግ ማለት ይህው ነውና፥ መንግሥተ ሰማያት የእኛ መሆኗን ነው የሚያረጋግጥልን።

ስለሆነም ቅዱስ ቃሉን ልብ ብለን ልናስተውለው ይገባናል ማለት ነው።

<u>ከዚህ ቀጥሎም</u> በመግቢያው እንደተገለጸው ጌታችን ወጥተው ወርደው እንዲያተርፉበት በጌታቸው ገንዘብ በተሰጣቸው ሰዎች ምሳሌ ያስተማረበትን ምሥጢር እናስታውሳለን።

አዎ በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 25፥14፥
በተመሳሳይም በሉቃስ ወንጌል 19፥12 ጀምሮ
እንደምንመለከተው፥

መንግሥተ ሰማያት ወጥተው ወርደው ያተርፉበት ዘንድ ብላቴኖቹን (ባሮቹን) ጠርቶ ገንዘቡን የሰጣቸው ነጋዴን ትመስላለች ይላል።

እነዚህ አገብርት (ባሮች) ወይም ደግሞ ብላቴኖች እየተባሉ የሚጠሩ ሰዎች ነግደው፣ ሠርተው እንዲያተርፉበት እንደየዐቅማቸው ታይቶ ለአንዱ አምስት፣ ለአንዱ ሁለት፣ ለአንዱም አንድ የተሰጣቸው ናቸው።

<u>(የሉቃስ ወንጌል</u> 19፥12 <u>አሥር ቢልም ምሥጢሩ አንድ ነው)</u>

አምስት የተቀበለ ወጥቶ ወርዶ ነግዶ ሌላ አምስትን አትርፎ ተገኘ። ሁለት የተቀበለም እንደዚሁ ወጥቶ ወርዶ ነግዶ ሌላ ሁለትን አትርፎ ተገኘ።

ባለ አንድ ግን የጌታውን ገንዘብ በጨርቅ ጠቅልሎ መሬት ቆፍሮ አኖረው።

ከጊዜም በኋላ ባለ ገንዘቡ ንብረቱ ውጤት ማስገኘቱን ለማወቅ ሊቆጣጠራቸው መጣ። ገንዘቡ በምን ሁኔታ ላይ እንዳለ ጠየቀ።

አምስት የተቀበለው አምስት ሰጥተኸኝ ነበር ሌላውን አምስት አተረፍሁበት ብሎ ዋናውንና ትርፉን ይዞ ወደ ጌታው ቀረበ። ጌታውም አንተ መልካም ታማኝ ቸር አገልጋይ (ባሪያ) ነህ፥ በጥቂት ታምነሃልና በብዙ ላይ እሾምሃለሁ ወደ ጌታህ ደስታም ግባ አለው።

ባለ ሁለቱም ልክ እንደባለ አምስቱ በጌታው የታመነና ወደ ጌታው ደስታ የሚገባ ሆነ።

ባለ አንድ ግን ወደ ጌታው ቀርቦ ጌታ ሆይ አንተ ካልዘራህበት የምታጭድ፣ ካልበተንህበትም የምትሰበስብ፣ ኃይለኛ ጨካኝ መሆንህን ስለማውቅ፥ እንዳይጠፋብኝ፣ ሌባ እንዳይሠርቀኝ፣ ወንበዴ እንዳይቀማኝ፣ ቀጣፊም እንዳያታልለኝ ብዬ ፈርቼ በጨርቅ ጠቅልዬ፣ መሬት ቆፍሬ ቀብሬ አኑሬው ነበር አሁን ግን ይህውልህ ገንዘብህ ተቀበለኝ ብሎ ዋናውን ብቻ ይዞ ቀረበ

ጌታውም አንተ ክፉና ሃኬተኛ ባሪያ እኔ ካልዘራህበት የማጭድ፥ ካልበተንህበትም የምሰበስብ ኃይለኛ ጨካኝ መሆኔን ታውቃለህን? ይህንማ ካወቅህ ገንዘቤን ወዲያውኑን ልትመልስልኝ (ልትሰጠኝ) በተገባህ ነበር እኔም ወጥቶ ወርዶ ነግዶ ለሚያተርፍበት በሰጠሁትና መጥቼም ያለኝን ከትርፉ ጋር በተቀጣጠርሁት ወይም ራሴ በሠራሁበት በማለት ያለውን ነጥቃችሁ ለባለ አምስቱ ስጡት ብሎ አዘዘ። እርሱን ክፉ ሃኬተኛውን ባሪያ ግን ወደ ጨለማ ውሰዱት አለ ይላል የወንጌሉ ቃል። <u>ማቴ 25፥14።</u>

አዎ እነዚህ ባለ አምስትና ባለ ሁለት አግብርት (ብላቴኖች) ታማኞች አገልጋዮች በተሰጣቸው ገንዘብ ጠንክረው ሰለ ሠሩ አትርፈው በመገኘታቸው ሲጠቀሙ፣ በጌታቸው በአምላካቸው በእግዚአብሔር ተመስግነው ወደ ገነት፣ ወደ መንግሥተ ሰማያት ሲገቡ፥ ክፉው ሃኬተኛው ባሪያ ግን የጌታውን ገንዘብ ቀብሮ ያለምንም ውጤት በማስቀረቱ በተሠጠው ገንዘብ ባለመሥራቱ፣





ባገኘው ዕድል ባለመጠቀሙ ተጐዳ። በጌታው በእግዚአብሔር ተወቅሶ ወደ ሲኦል፣ ወደ ገሃነመ እሳት ሐድ ተባለ ማለት ነው።

አዎ ይህ ዐቢይ ምሥጢርና ዋና መልእክቱ ሁላችንንም ይመለከታል።

ይኸውም በትርጓሜው መሠረት ሲብራራ መምህራን ካህናት ተምረውካላስተማሩ፣ በተሰጣቸው ዕውቀት ካልሠሩበት ካላቸው መንፈሳዊ ደርጃ ወርደው በተራ ሰዎች ቦታ እንደሚሆኑ፥ ማለትም፥ በሰማይና በምድር ትልቅ መብት ያለውን የክህነት መዓርጋቸውን (ሹመታቸውን) እንደሚገፈፉ፥ ክህነታዊ ክብራቸው ቀርቶ ከተራ ሰዎች ጋር እንደሚመደቡ፣ እንደ ባለ አንዱ በጌታችን እንደሚወቀሱና ሒዱ ተብለውም ወደ ጨለማ እንደሚባረሩ፥ አስተምረው መክረው ራሳቸውን አስመስለው የሚተኩ ደግሞ እንደባለ አምስትና እንደባለ ሁለት በክብር ላይ ክብር እንደሚጨመርላቸው ወደ ገነት፣ ወደ መንግሥተ ሰማያትም እንደሚገቡ ሲያስረዳን። ምእመናንም ከእግዚአብሔር በተሰጣቸው ሙሉ አካልና ሀብት የጽድቅን ሥራ ካልሠሩበት፣ ካልመጸወቱ ካልጾሙ፣ ካልጸለዩ፥ በሁሉም ችግራቸው እየተረዳዱ በእውነተኛው ፍቅር አንድ ሆነው ካልኖሩ እንደ ባለአንዱ ይወቀሳሉ ሥፍራቸው በጨለማ ውስጥ ይሆናል፣ ሒዱ ተብለውም ወደ ገሃነመ እሳት ይባረራሉ ማለት ነው።

<u>በአጠቃላይ</u> ይህ ቃል ሁላችንም ባገኘነው ዕውቀት ካላስተማርንበት በምንችለው ዐቅም ሁሉ መልካሙን ሥራ ካልሠራን፣ እንደ እኛ መሥራት የማይችሉት ደካሞች ወገኖችን ከእግዚአብሔር በተሰጠን ሙሉ አካል ወጥተን ወርደን ካልረዳን፣ ከምናገኘው ሁሉ አሥራትንና በኵራትን ካላወጣንበት በዓለም ፍጻሜ፥ ማለትም፥ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በግርማ መንግሥቱ መጥቶ ጻድቃንን በሚቀበልበት፣ ኃጥኣንን በሚያሰናብትበት ጊዜ እንደ ባለ አንዱ ተወቅሰን እንደምንባረር ወደ መንግሥተ ሰማያትም መግባት እንደማንችል ነው አስቀድሞ እያስጠነቀቀን ያለው።

ስለሆነም በበጎች የሚመሰሉ ጻድቃን በቀኙ፣ በፍየሎች የሚመሰሉ ኃጥኣንም በግራው ቆመው የመጨረሻው ፍርድ በሚፈረድበት ሰዓት ለመንግሥተ ሰማያት እንድንበቃ፥ በእምነታችን ጸንተን፥ እየጾምን፣ እየጸለይን፣ እየመጸወትን፣ በትሕትና፥ በርኅራኄና በትዕግሥት፣ በእውነተኛው ፍቅር አንድ ሆነን እየተረዳዳን፥ ኃጢአታችንን እየተናዘዝን፥ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙንም እየተቀበልን መኖር ይገባናል ማለት ነው። <u><<ጌታው በቤተ ሰዎቹ ላይ የሾመው ታማኝና ልባም ባሪያ ማን ነው? ማቴ 24፥45 >></u>

# ክፍል 37፥

## <<ኒቆዲሞስ የዐቢይ ጾም 7ኛ እሑድ>>

የዐቢይ ጾም 7ኛ እሑድ፣ ሳምንቱም ኒቆዲሞስ ይባላል።

ከኒቆዲሞስ ቀጥሎ ያለው ሳምንት ሆሣዕና ሲሆን፥ ከሰኞው ጀምሮም ሕማማት ይሆናል፥ ከዛም በመጨረሻው ዓርብ ስቅለት፥ በ3ኛው ቀን እሑድ ደግሞ ትንሣኤ ክርስቶስ ነው ማለት ነው።

የዐቢይ ጾሙ 7ኛ እሑድ ኒቆዲሞስ የተባለ የአይሁድ አለቃ የነበረ ፈሪሳዊ በሌሊት ወደ ጌታችን እየሔደ እየሰገደ ምሥጢረ መጻሕፍትን ሲማር መኖሩን የምናስታውስበት ዕለት ነው።

በቅዱስ ዮሐንስ ወንጌል እንደምንመለከተው፥ በሀብት በዕውቀትና በሹመት የላቀ ከፈሪሳውያን ወገን የሚሆን ኒቆዲሞስ የተባለ የአይሁድ አለቃ የነበረ መምህር በሌሊት ወደ ጌታችን ሔዶ ሊቀ መምህር ሆይ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ከሆነ ከአንተ በስተቀር አንተ የምታደርጋቸውን ተአምራት የሚያደርግ ከቶ ማንም የለምና አንተ ልታስተምር ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደመጣህ እናውቃለን አለው።

ጌታችንም እውነት እውነት እልሃለሁ ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት አያይም፡ የሚል ድንገተኛ የሆነውን ምሥጢር ነገረው። ዮሐ 3፥1።

በትርጓሜው መሠረት እንደምንገነዘበው ኒቆዲሞስ ወደ ጌታችን ሔዶ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ከሆነ ከአንተ በስተቀር አንተ የምታደርጋቸውን ተአምራት የሚያደርግ ከቶ ማንም የለምና ልታስተምር ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደመጣህ እናውቃለን ማለቱ ጌታችን ምሥጢሩን ስለገለጸለት እግዚአብሔር አብ በህልውና ከእርሱ ጋር ካለ ከአንተ በቀር እንደዚህ ያለውን አምላካዊ የሆነ ድንቅ ሥራን ሊሠራ የሚችል ከቶ ማንም የለምና አንተ ከእግዚአብሔር አብ፣ አካል ዘእምአካል ባሕርይ ዘእምባሕርይ ተወልደህ ልታስተምር፣ ዓለምን ልታድን እንደመጣህ እናውቃለን ሲለው፥ ፈጣሪው እግዚአብሔር በገለጸለት መሠረት አንድነቱን ሲናገር ነው ማለት ነው።





ጌታችንም <<አማን አማን እብለከ ዘኢተወልደ ዳግመ እማይ ወእመንፈስ ቅዱስ ኢይክል በዊአ ውስተ መንግሥተ እግዚአብሔር>>

እውነት እውነት እልሃለሁ ዳግመኛ ከውሃና ከመንፈስ ቅዱስ፥ (ከአብራክ መንፈስ ቅዱስ ከማኅፀነ ዮርዳኖስ) ያልተወለደ፥ ማለትም ተምሮ ተረድቶ አምኖ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም፣ በውሃ ያልተጠመቀ ወደ መንግሥተ እግዚአብሔር አይገባም አለው።

<<ዘኢተወልደ ዳግመ እማይ>>

ዳግመኛ ከውሃ ያልተወለደ ብሎ እግዚአብሔር ወልድን፣

<<ወእመንፈስ ቅዱስ>>

ከመንፈስ ቅዱስ ብሎ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን፣

<<መንግሥተ እግዚአብሔር>>

መንግሥተ እግዚአብሔር ብሎም፥ እግዚአብሔር አብን፥ አስተምሮታል።

በአጠቃላይ ምሥጢረ ሥላሴንና ምሥጢረ ጥምቀትን በምሳሌ አድርጎ በሚገባ ገልጾለታል ማለት ነው።

<<ምሥጢሩ በአበው ትርጓሜ መሠረት ሲብራራ ነው>>

ከዚህ በኋላ ኒቆዲሞስ የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋይ ሆነ ጌታችን በመስቀል በተሰቀለ ጊዜም ከዮሴፍ ጋር በመሆን በክብር ገንዞ ቀበረው።

አዎ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምሥጢረ ሥላሴንና ምሥጢረ ጥምቀትን፥ ማለትም የእግዚአብሔርን አንድነትንና ሦስትነትን ተምሮ አውቆ አጻኝነቱን ተረድቶ፥ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ያልተጠመቀ ወደ መንግሥተ እግዚአብሔር (መንግሥተ ሰማያት) መግባት እንደማይችል ለሁላችንም በዚሁ ምሥጢር አረጋግጦልናል ማለት ነው።

# ምዕራፍ 10፥

# ሆሳዕና በአርያም፥

ሆሳዕና ማለት በግእዝ ቋንቋ በቀጥታ ሲተረጉም መድኃኒት ማለት ሲሆን፥ በሮማይክ ቋንቋም የጌታችን ስም ሆኖ አሁን አድን አሁን ርዳ ማለት እንደሆነ ይነገራል።

<<ሆሳዕና በአርያም>> ስንል፥ በሰማይ ያለ፣ ከሰማይ የወረደ (የመጣ) መድኃኒት ኢየሱስ ክርስቶስ የተመሰገነ ነው ማለታችን ነው።

አዎ ሆሳዕና፥ ፍጹም መድኃኒታችን የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ከደብረ ዘይት (ከቢታንያ) ወደ ቅድስት ሀገር ወደ ኢየሩሳሌም ሲገባ << ሆሳዕና በአርያም ለወልደ ዳዊት>> በሰማይ ያለ መድኃኒት የዳዊት ልጅ የእስራኤል ንጉሥ እየተባለ በደማቅ መልክ አቀባበል የተደረገበትን፣ የተመሰገነበትንና ልዩ ልዩ ተአምራትንም ያደረገበትን ምሥጢር በማስታወስ የምናከብረው ሃይማኖታዊና መንፈሳዊ በዐላችን ነው።

ይህን ዐቢይ ምሥጢር ነቢዩ ዘካርያስ አስቀድሞ፥ <<አንቺ የጽዮን ልጅ ሆይ እጅግ ደስ ይበልሽ፥ አንቺ የኢየሩሳሌም ልጅ ሆይ ዕልል በዪ፥ እነሆ ንጉሥሽ ጻድቅና አዳኝ ነው፤ ትሑትም ሆኖ በአህያና በአህያይቱ ግልገል በውርንጫይቱ ላይ ተቀምጦ ወደ አንቺ ይመጣል>> ብሎ በትንቢቱ ገልጾታል። ዘካ 9፥9።

ትንቢቱና ምሳሌው በሌሎች ቅዱሳት መጻሕፍትም ተዘግቦ እናገኘዋለን።

በተለይም ደግሞ በኢሳይያስ ምዕራፍ 52፥1, 60፥1 እና በመዝሙር 8፥2፥ እንዲሁም በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 12፥12 ጀምሮ እንደምንመለከተው፥ ጌታችን ከደብረ ዘይት (ከቢታንያ) ወደ ቅድስት ሀገር ወደ ኢየሩሳሌም በገባ ጊዜ፥ ሕዝቡ፥ ማለትም አረጋውያን፣ ወጣቶችና ሕፃናት የሰሌን ዛፍ ዝንጣፊን ይዘው ሆሳዕና በአርያም እያሉ ሲቀበሉት ጽዮን (ኢየሩሳሌምም) በእግዚአብሔር ምስጋና፣ በዕልልታና በጭብጨባ ደምቃ ነበር።





ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከፋሲካው 6 ቀን አስቀድሞ ከሙታን ያስነሣው አልዓዛር ወደ ነበረበት ወደ ቢታንያ ሔደና በዚያው ራት ተደረገለት።

ማርያም እንተ ዕፍረት አስቆሮታዊው ይሁዳ ይህ ሽቱ ተሽጦ ለነዳያን ቢመጸወት ይሻል ነበር በማለት በሁኔታው ያኮረፈበት፥ ከዚያም አልፎ ከሽያጩ ሊያገኘው ይችል የነበረው ጥቅም ስለ አልተሳካለት ተናዶ ጌታውን ለመሸጥ ምክንያት አድርጎ የተነሣሳበት፣ ዋጋው ከፍ ያለ በጣም የተወደደና የከበረ፥ ልዩና መልካም የሆነ መዓዛ ያለውን ሽቱ ጌታችንን እግሩን የቀባችበት ጊዜ ማለት ነው።

ከዚህ ራት በኋላ ጌታችን ወደ ቅድስት ሀገር ወደ ኢየሩሳሌም እንደመጣ ስለ ተሰማ ሕዝቡ፥ አረጋውያንና ወጣቶች፥ ሕፃናትም ጭምር የሰሌን ዛፍ ዝንጣፊን ይዘው፥

## <<ሆሳዕና በአርያም ለወልደ ዳዊት ቡሩክ ዘይመጽእ በስመ እግዚአብሔር ወንጉሦሙ ለእስራኤል>>

በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ በሰማይ ያለ መድኃኒት የዳዊት ልጅ፣ የእስራኤል ንጉሥ የተባረከ ነው። በማለት በደማቅ ዕልልታና በልዩ ልዩ ምስጋና ተቀበሉት።

የቢታኒያ ድንጋዮችም በልሳነ ሰብእ (እንደ ሰው አፍ አውጥተው) እንዳመሰገኑት ይነገራል።

ከዚህ በላይ ከፍ ብሎ እንደ ተጠቀሰው አስቀድሞ የተነገረው ትንቢት በዚሁ ጊዜ ተፈጸመ ማለት ነው።

ጌታችን ወደ ቅድስት ሀገር ወደ ኢየሩሳሌም በገባበት ሰዓት፥ ፍጹም ሕይወትን ለማግኘት ሲሉ ፈጣሪያቸውን በጸሎት እየተማፀኑ በእርሷ ተጠግተው የሚኖሩትን ሕሙማን ፈውሶ በቤተ ክርስቲያን (በቤተ መቅደሱ) ሊፈጸም የማይገባውን በማስወገድ፤ እውነተኛውን ትምሕርቱን አስተምሮ፣ መመሪያውንም ሰጥቶ፤ በዘመኑ ምኩራብ በመባል የምትታወቀው ምሕረትንና ይቅርታን ከእግዚአብሔር የሚለመንባት ቤተ ክርስቲያን (ቤተ መቅደስ) ለፍጹም ሕይወት፣ ለጸሎት የመረጣት ልዩ የምስጋና ቤት መሆኗን አረጋግጧል።

በመሆኑም ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ይህን መሠረት በማድረግ ጥንታዊ ሥርዓቱን በመጽሐፋዊ ትውፊት ከአበው ተቀብላ ሃይማኖታዊ ታሪኩንና መንፈሳዊ ባህሉን ጠብቃ በእየዓመቱ በደማቅ መልክ እያከበረችው ትገኛለች።

2ኛ በሰኑይ (ሰኞ) ዕለት ከምድር እስከ ሰማይ ድረስ ሞልቶ የነበረው ውሃ ከሦስት ከፍሎ በየሥራው መድቦታል።

3ኛ በሠሉስ (ማክሠኞ) ዕለት ሣርና ዕፀዋት ተፈጥረዋል።

4ኛ በረቡዕ (ሮብ) ዕለት ፀሐይ፣ ጨረቃና ከዋክብት ተፈጥረዋል።

5ኛ በሐሙስ ዕለት በልባቸው የሚሳቡ፣ በዕግራቸው የሚሽከረከሩ፣ በክንፋቸው የሚበሩ በደመ ነፍስ ሕያዋን ሆነው የሚኖሩ ፍጥረታት ተፈጥረዋል።

6ኛ በዓርብ ዕለት በኵረ ፍጥረታት (የፍጥረታት በኹር የሚባለው አዳም ተፈጥሯል) ዓርብ የፍጥረት መጨረሻ ናት። ከዚህ በኋላ አልፈጠረም።

ስለሆነም፥

7ኛ ቅዳሜ ጌታችን ፍጥረቱን ሁሉ ፈጥሮ ደምድሞ ዕረፍቱን ያደረገባት የዕረፍት ቀን ናት ማለት ነው።
(አሪት ዘፍጥረት ከምዕ 1፥1 ጀምሮና መጽ. ኩፋሌ 2፥1 ጀምሮ በሰፊው እንመልከት)

<<ከአበው የዓርብ ውዳሴ ማርያም ትርጓሜም የተጠቀሰ ነው>>

ሰሙነ ሕማማት በቤተ ክርስቲያናችን ልዩ ትኩረት የሚሰጥባት ሳምንት ናት።

ሰሙነ ሕማማት (የሕማማት ሳምንት) ከዚህ በስተመጨረሻ የተጠቀሱት የቅዱሳት መጻሕፍት መግለጫዎች እንደሚያስረዱን፥

ሰኞና ማክሠኞ አይሁድ ጌታችንን ለመያዝ የመከሩባቸው ቀናት ሲሆኑ፥

ሮብ ደግሞ እንዴት አድርገው እንደሚይዙት ምክራቸው ተሳክቶላቸዋልና። ሐሙስ እንዳይዙት ፋሲካቸው በመሆኑ ከሕዝብ ሁከት እንዳይነሣባቸው ፈርተው፥ በበዐላቸው ምክንያት ሐሙስን አሳልፈው፥ ዓርብ ዕለት በመከሩትና በወሰኑት መሠረት





በአስቆሮታዊው በይሁዳ አማካይነት ይዘውት የተለያየውን ግፍ ሲፈጽሙበት ከዋሉ በኋላ በመጨረሻው ጊዜ ሰቀሉት።
ዮሐ 11፥46, 19፥17, ሉቃ 23፥26

ሰሙነ ሕማማት በቤተ ክርስቲያን እየተገኘን ምንም በደል ሳይኖረው ስለ እኛ ስለ በደለኞች ሲል የተቀበለውን የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ፀዋትወ መከራ እያሰብን ስለ ስርየተ ኃጢአት የምንጸልይባትና የምንሰግድባት ሳምንት ስትሆን በተለይም ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ከጸሎተ ሐሙስ በፊት ያሉትን ሦስቱን ቀናት፥ ማለትም ሰኞን፣ ማክሠኞንና ሮብን የ5500 ዘመን፥ የፍዳን፣ የመርገምንና የጨለማን ምሳሌ አድርጋ እንደምትቆጥራቸው ይገለጻል።

አዎ ሰሙነ ሕማማት ሰሙኑን ሙሉ በቤተ ክርስቲያን እየተገኘን ጌታችን ምንም በደል ሳይኖረው ስለ እኛ ሲል የተቀበለውን ልዩ ልዩ ፀዋትወ መከራን እያሰብን በጾም፣ በጸሎት፣ በስግደት፣ በኀዘንና በልቅሶ ልናሳልፋት የሚገባን ልዩ የሆነች የሱባኤ ሳምንት ናት።

## ክፍል 39፥

## ሐሙስ፣ ጸሎተ ሐሙስ፥ (የሐሙስ ጸሎት)

ጸሎተ ሐሙስ ጌታችን የጸለየባት፣ የሰገደባት፥ የሐዋርያትን እግር በማጠብ ትሕትናን በተግባር ያስተማረባት ዕለት ስትሆን፥ በተለይም ደግሞ የሐዲሱን ምሥጢረ ቍርባን ለሐዋርያት ያሳየባት፥ ይህ ሥጋዬ ነው ይህም ደሜ ነው ብሎ ሥጋውን በስንዴ፣ ደሙንም በወይን አድርጎ ይህን ያልበላ፣ ይህንንም ያልጠጣ ሕይወት የለውም በማለት ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን የሰጠባት፥ ሐዲስ ምሥጢርም የተገለጸባት ዕለት ናት።

(ጸሎተ ሐሙስ ማለት የሐሙስ ጸሎት ማለት ሲሆን ምሥጢሩም ከላይ የተገለጸው ነው)

ጥቅስ <<ሲበሉም ኢየሱስ እንጀራን (ዳቦውን) አንሥቶ ባረከ፣ አከበረ፣ ለወጠ፥ ቆርሶም ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠና፥ ነገ በመልዕልተ መስቀል የሚሰዋው ሥጋዬ ይህ ነው እንካችሁ ብሉ አለ። ጽዋውንም አንሥቶ አመስግኖም ሰጣቸው እንዲህም አለ ሁላችሁ ከርሱ ጠጡ ስለ ብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የሐዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው>>(ማቴ 26፥26)

አዎ ጌታችን በጸሎተ ሐሙስ፥ ማለትም በስቅለቱ ዋዜማ ኅብስቱንና ወይኑን ባርኮ፣ ቀድሶ፣ ፈትቶ፥ እንካችሁ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው። ሁላችሁም ከእርሱ ጠጡ። ይህ ስለ ብዙዎች የኃጢአት ስርየት የሚፈስ የሐዲስ ኪዳን ደሜ ነው ብሉ ለደቀ መዛሙርቱ ለሐዋርያት ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን ሰጥቶአቸዋል። የሐዲስ ኪዳን ምሥጢረ ቍርባንንና ሥርዓቱንም ሁሉ አሳይቶአቸዋል።

<u>በተጨማሪም እነዚህን ጥቅሶች እንመልከታቸው፥</u>

<u>1ኛ</u> ኢየሱስ (ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፣ እግዚአብሔር ወልድ ማለት ነው)፥ አብ (የባሕርይ አባቱ እግዚአብሔር አብ ማለት ነው) ሁሉን በእጁ እንደ ሰጠው ከእግዚአብሔርም እንደ ወጣ ወደ እግዚአብሔርም እንዲሔድ አውቆ ከራት ተነሣ ልብሱንም አኖረ። ማበሻም ጨርቅ ወስዶ ታጠቀ በኋላም በመታጠቢያው ውሃ ጨመረ የደቀ መዛሙርትንም እግር ሊያጥብና በታጠቀበት ማበሻ ጨርቅ ሊያብስ ጀመረ። (አዎ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትሕትናን በተግባር አስተማረ) <u>ዮሐ 13፥3።</u>

<u>2ኛ</u> በሩ እኔ ነኝ፣ በእኔ የሚገባ ቢኖር ይድናል፣ ይገባልም፣ ይወጣልም። <u>ዮሐ 10፥9</u>

(ወደ መንግሥተ ሰማያት ይገባል <<ይጸድቃል>> ማለት ነው)።

<u>3ኛ</u> የሕይወት ምግብ (እንጀራ) እኔ ነኝ፥ ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይራብም፣ በእኔ የሚያምንም ለዘለዓለም አይጠማም። <u>ዮሐ 6፥35</u>

<u>(ጌታችን ስለ ብዙ ሰዎች የሚፈስ የሐዲስ ኪዳን ሥርዓት ደሜ ይህ ነው ንሡ አላቸው) ማር 14፥22, 1ኛ ቆሮ 11፥23 ጀምሮ</u>

<u>4ኛ</u> ጌታችን በአይሁድ ከመያዙ በፊት እንደጸለየና ትጉ ጸልዩም እንዳለ <u>በማቴ 26፥36,</u> በተመሳሳይም <u>በማር 14፥32,</u> <u>በሉቃ 22፥39</u> እና <u>በዮሐ 17፥1</u> እናገኘዋለን።

በመሆኑም ትምህርቱ ሁላችንንም ስለሚመለከት ተግተን መጸለይ ይገባናል ማለት ነው።





## <u>ክፍል 40፥</u>

## <u>በሰሙነ ሕማማት ውስጥ ዓርብ ስቅለት፥</u>

ዓርብ ማለት ከላይ እንደተጠቀሰው የፍጥረት መካተቻ (መደምደሚያ) ማለት ነው።
ምክንያቱም ጌታችን እስከ ዓርብ ድረስ ፍጥረቱን ሲፈጥር ሰንብቶ ዓርብ ፍጥረቱን ሁሉ ፈጥሮ ስለ ደመደመ የፍጥረት መካተቻ ወይም መደምደሚያ ትባላለች።

እንዲሁም ሕዝበ እስራኤል እስከ ዓርብ ድረስ መና እየዘነመላቸው ሲለቅሙ ሰንብተው በዓርብ ስለሚጨርሱ፣ ዓርብ የቅዳሜንም ጭምር ደርበው ስለሚከቱ (ስለ ሚሰበስቡ) የመና መካተቻም እየተባለች ትጠራለች ማለት ነው።
<u><<ከአበው ትርጓሜ የዓርብ ውዳሴ ማርያም>></u>

<u>ዓርብ፥</u> ዓርብ ስቅለት መባሏም ጌታችን የተሰቀለባት ቀን ስለ ሆነች ነው።

<u>ሰሙነ ሕማማት</u>፥ ከዚህ በላይ እንደተገለጸው አይሁድ ጌታችንን ለመያዝ <u>ሰኞና ማክሠኞ</u> ተሰብስበው መክረው ባይሳካላቸውም ሮብ ምክራቸው ስለ ተሳካ <u>ሐሙስ</u> የፋሲካ በዐላቸውን አክብረው <u>ዓርብ መጋቢት 27 ቀን</u> በአስቆሬታዊው በይሁዳ አማካይነት ይዘውት አስረው ወስደው ከዘመኑ ገዥ ከጲላጦስ ፊት አቅርበው ካስገረፉት በኋላ በግፍ ስለ ሰቀሉት ዘጠኝ ሰዓት ሲሆን በገዛ ሥልጣኑ ቅድስት ነፍሱን ከክቡር ሥጋው ለይቶ፣ መለኮት በአካለ ነፍስ ወደ ሲኦል ወርዶ፣ አስቀድሞ ለአዳም በሰጠው የድኅነት ተስፋ መሠረት ከአዳም ጀምሮ እስከ ዚያች ቀን ድረስ በሲኦል ውስጥ ተግዘው የነበሩትን ነፍሳት አውጥቶ ወደ ገነት አስገባቸው።

<u>አዎ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ፥</u> ክርስቶስ ደግሞ ወደ እግዚአብሔር እንዲያቀርበን እርሱ ጻድቅ ሆኖ ስለ ዓመፀኞች አንድ ጊዜ በኃጥአት ምክንያት ሞቶአልና፥ በሥጋ ሞተ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ። በእርሱም ደግሞ ሔዶ በወኅኒ ለነበሩት ነፍሳት ነጻነትን ሰበከላቸው እንዳለው። <u>1ኛ ጴጥ 3፥18</u> ጌታችን ወደ እርሱ ሊያቀርበን፣ ከራሱ ጋር ሊያስታርቀን ስለወደደ በለበሰው ሥጋ በፈቃዱ ሞቶ ለእኛ ግን ፍጹም ሕይወትን ሰጠን።

በዕለተ ዓርብ ጌታችን በተሰቀለ ጊዜ ብዙ ተአምራትም ተደርጓል።

ለምሳሌ፥ ምድር ተናውጣለች፣ ፀሐይ ጨልሞአል፣ ጨረቃ ደም ሆኖአል፣ ከዋክብት እንደ ቅጠል ረግፈዋል፣ አዕባን (ድንጋዮች) ተፈትተዋል (ደቅቀዋል) የምኵራቡ (የቤተ ጸሎቱ) መጋረጃም ከላይ አንሥቶ እስከ ታች ድረስ ከሁለት ተሰንጥቋል (ተከፍሎአል) መቃብራት ተከፍተዋል፣ ሙታንም ተነሥተዋል። ማቴ 27፥51, ማር 15፥37።

## ክፍል 41፥

## የዓርብ ስቅለት ጥብጣቤ፣ የንስሓውና የስግደቱ ምሥጢር፥

የዕለተ ዓርብ ጥብጣቤ ከላይ በሰፊው እንደተገለጸው ጌታችን ለእኛ ሲል ስለ ተገረፈ ግርፋቱን በማስታወስ፥ በሥጋችን መከራን ችለን ታግሠን ፈተናውን ካለፍን ፍጹም ሕይወትን እንደምናገኝ የሚያመለክት ሲሆን፥ ንስሓውና ስግደቱም አሁን እንደተነገረው ከምሥጢሩ ጋር የተያያዘ ሆኖ፥ በውስጡ ሁላችንም ንስሓን እየገባን፣ እየሰገድን ከኃጢኣት ከበደል ሁሉ ንጹሓን መሆን እንደሚገባን የሚያስገነዝበን ትምህርታዊ መልእክት ያለበት ነው።

ዓርብ ከጥንት፥ አዳም የተፈጠረባት፣ ከገነትም የወጣባት ስትሆን፥ በሐዲስ ዘመን በአሁኑ ደግሞ ጌታችን የተሰቀለባት፥ በመጨረሻም ፍጹም ሕይወትን የሰጠባት፣ ነፍሳትን ከሲኦል ወደ ገነት ያስገባባት፣ እኛን ያዳነባት፣ ሞትና ሕይወት የታየባት፣ ሌሊትና ቀን (ጨለማና ብርሃን) የተፈራረቀባት፥ በነቢያት የተነገረው፣ በልዩ ልዩ ቅዱሳት መጻሕፍት የተዘገበው ትንቢት የተፈጸመባት በመሆኗ በቤተ ክርስቲያናችን ሃይማኖታዊና መንፈሳዊ ታሪክ ለየት ያለ ሥፍራ አላት።

ሕዝበ እስራኤል በመልአኩ በቅዱስ ሚካኤል ተራዳኢነትና መሪነት፣ በነቢዩ ሙሴ አስተባባሪነት ከግብፅ ክፉ አገዛዝ ነጻ ወጥተው የኤርትራን ባሕር በተሻገሩ ጊዜ የጠላታቸውን ስጥመትንና የእግዚአብሔርን ድንቅ የሆነ አምላካዊ ሥራ ተመልክተው የተመሰገነውን እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን





በማለት ከጠላታቸው ያዳናቸውን፣ የኤርትራን ባሕር ከሁለት ከፍሎ በሰላም ያሻገራቸውን ፈጣሪያቸው እግዚአብሔርን እንዳመሰገኑት። ዘፀ 15፥1, መዝ 135፥10

እኛ የክርስቶስ ወገኖች ሕዝበ ክርስቲያንም በቅዱሳት መጻሕፍት እና በሃይማኖታዊ ትውፊት (ቅብብሎሽ) በተረከብነው መንፈሳዊ ሥርዓት መሠረት፥ በየዓመቱ ዓርብ ስቅለት በቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን እየተገኘን ጌታችን ምንም በደል ሳይኖረው ስለእኛ ስለበደለኞች ሲል የተቀበለውን ልዩ ልዩ ፀዋትወ መከራ እያስብን፥ ስለ ኃጢኣታችን ስርየት እየሰገድን ውለን ሠርክ ሲሆን ደግሞ ድኅነታችንን በማስታወስ ባሕረ እሳት ያሻገረንን፣ ከዲያብሎስ የባርነት ግዛት ነጻ ያወጣንን፣ ከሞተ ኃጢኣት ያዳነን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን፥

## <<ንሴብሖ ለእግዚአብሔር ስቡሐ ዘተሰብሐ>>

የተመሰገነውን እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን በማለት ይህን ያደረገልን አምላካችንን በክብርና በጸናጽል ስናመሰግን እንኖራለን።

አዎ አስቀድሞ በትንቢት ተነግሮ፣ በቅዱሳት መጻሕፍት በየክፍሉ ተዘግቦ እንደምናገኘው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለአዳም በሰጠው የማይሻር የሕይወት ተስፋ መሠረት ዘመኑ ሲደርስ እንደ እኛ አቈጣጠር በ5500 ዓመተ ዓለም ፍጻሜ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ በ5533 ዓመተ ዓለም (በ33 ዓመተ ምሕረት) በዘመነ ቅዱስ ማርቆስ መጋቢት 27 ቀን በመስቀል ተሰቅሎ ዓለምን አዳነ።

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ከጽኑዕ ፍቅሩ የተነሣ ጌታችንን ሞትስ አይገባህም እንዳለው እኛም ጌታችን ባይሞት እንወድ ነበር።

ነገር ግን ምንም እንኳን ሞት የማይገባው የባሕርይ አምላክ ቢሆንም እርሱ ሞቶ ካላዳነን እኛ ሁላችን ፍጹም ሕይወት ሊኖረን ስለማይችል፥ ለፍጹም ሕይወታችን ሲል በፈቃዱ በለበሰው ሥጋ ሞቶ ፍጹም የሆነውን ሕይወት ሰጠን። ማቴ 16፥21

አዎ ሰው ምንም እንኳን በእግዚአብሔር አርአያና አምሳል የተፈጠረ ልዩ ክቡር ፍጥረት ቢሆንም፥ አስቸጋሪና ደካማ የሆነ ባሕርይ ያለበት እንደመሆኑ መጠን፥ የፈጣሪውን ሕግንና

ከእንግዲህ በኋላ እኛ ራሳችን በከፉ ተግባራችን እንደገና ካልገነባነው በስተቀር ቀድሞ የነበረው መርገምና የውርስ ኃጢአት በክርስቶስ መስቀል ተደምሷል፣ ሸክማችን ቀልሏል፣ በክርስቶስ ቤት መልካም የሆነ ማረፊያ ተዘጋጅቶልናል። ማቴ 11፥29

በተጨማሪም ከዚህ ቀጥለው ያሉትን ጥቅሶች እንመልከታቸው፥

1ኛ <<እግዚአብሔርሰ ንጉሥ ውእቱ እምቅድመ ዓለም>> እግዚአብሔርስ ከዓለም (ከፍጥረት ሁሉ) አስቀድሞ ንጉሥ ነው፣ በምድርም መካከል መድኃኒትን አደረገ። መዝ 73፥12። ይህ ቅዱስ ቃል እግዚአብሔር ምንም እንኳን እኛን ለማዳን ሲል በለበሰው ሥጋ መራራውን ሞት ቢቀምስም በመለኮቱ ግን የማይሞት ሕያው የባሕርይ አምላክ፥ የነበረ፣ ያለ፣ ፍጥረታትን ሁሉ አሳልፎ የሚኖር ፈጣሪ መሆኑን ነው የሚገልጽልን።

2ኛ በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ፣ ሕማማችንንም ተሸከመ..... ስለ በደላችንም ደቀቀ፣.....የደኅንነታችንም ተግሣፅ በእርሱ ላይ ነበረ፣ በእርሱ ቊስል እኛ ተፈወስን፣ የሁላችንንም በደል በእርሱ ላይ አኖረ። ኢሳ 53፥4

3ኛ <<የተጠራችሁት ለዚህ ነውና ክርስቶስ ደግሞ ፍለጋውን እንድትከተሉ ምሳሌን ትቶላችሁ ስለ እናንተ መከራን ተቀብሏልና እርሱ ኃጢአትን አላደረገም፣ ተንኮልም በአፉ አልተገኘበትም። ሲሰድቡት መልሶ አልተሳደበም፣ መከራንም ሲቀበል አልዛተም። ነገር ግን በጽድቅ ለሚፈርደው ራሱን አሳልፎ ሰጠ። ለኃጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር እርሱ ራሱ በሥጋው ኃጢአታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ በመገረፉ ቊስል ተፈወሳችሁ>> 1ኛ ጴጥ 2፥21 ጀምሮ ይህ ቅዱስ ቃል ጌታችን ስለ እኛ ሲል የተቀበለውን ፀዋትወ መከራን፣ ትዕግሥቱንና ትሕትናውን በመግለጽ እኛም የእርሱን መልካም ሥራ እንድንከተል ነው እያስተማረን ያለው።

4ኛ <<በክርስቶስ እንዳች ምክር ቢሆን፣ የፍቅር መጽናናት ቢሆን፣ የመንፈስ ኅብረት ቢሆን፣ ምሕረትና ርኅራኄም ቢሆኑ፥ ደስታዬን ፈጽሙልኝ በአንድ አሳብም ተስማሙ>> ፊልጵ 2፥1 ጀምሮ ይህም ጌታችን ያ ሁሉ ፀዋትወ መከራ የተቀበለውና የተሰቀለውምንም ልዩነትን ሳያደርግ ለመላ ዓለም እንደ





መሆኑ መጠን፣ እኛ ሁላችንም በክርስቶስ አንድ ክርስቲያን ሆነን በእውነተኛው ፍቅር ተስማምተን እየተረዳዳን እንድንኖር ነው እየመከረን ያለው ይኸውም ትሕትናን፣ ርኅራኄንና እውነተኛውን ፍቅር ገንዘብ አድርገን በጽድቁ መኖር እንደሚገባን፥ በክርስቶስ ነፃ ስለወጣን ተመልሰን ወደ ኃጢአት ባርነት፣ ወደ ዲያብሎስ ክፉ አገዛዝ እንዳንገባ ብርቱ ጥንቃቄን ማድረግ እንዳለብን ነው የሚያስገነዝበን።

<<ጥቅሶቹ ከልዩ ልዩ ክፍል የአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ የተወሰዱ ናቸው>>

እንዲሁም ማቴ 27፥1 ጀምሮ, በተመሳሳይም ማር 14፥1ጀ ምሮ,ሉቃ 22፥1 ጀምሮ እና ዮሐ 17፥1 ጀምሮም ቀስ ብለን እንመልከት፥

ይህን ላደረገልን ለእግዚአብሔር አምላካችን ምስጋና ይድረሰው።

# ምዕራፍ 12፥

# ቅዳሜ ሥዑር፥

ቅዳሜ ሥዑር ማለት፥ ቅዳሜና እሑድ የማይጾሙ ሲሆኑ፥ በጌታችን ስቅለት ማግሥት ቅዳሜ ግን ጌታችን በከርሠ መቃብር በማደሩ ምክንያት ቀዳሚት (ቅዳሜ) በአክፍሎት እንድትጾም በቤተ ክርስቲያናችን የጾም ሥርዓት ፍትሐ መንፈሳዊ ስለታዘዘ ትጾማለችና የቅዳሜ ሥዑርነት ለመጾሟ ነው።

ዋናው ምሥጢሩ ደግሞ ቅዳሜ ሥዑር ማለት በቅዱሳት መጻሕፍት እንደተዘገበው፥ <<ሠዓሮ ለሞት>> ይላል በግእዙ ሲጠቀስ ጌታችን ሞተ ኃጢአትንና ዲያብሎስን ሽሮ ፍዳንና መርገምን ሁሉ ደምስሶ ፍጹም የሆነውን ሕይወት ስለሰጠን ይህን ያንፀባርቃል።

በቅዳሜ ሥዑር ለሁሉም ለምለም ቄጤማ (ሣር) እየታደለ የምሥራች ይባላል።

ይኸውም፥

## <<ገብረ ሰላመ በመስቀሉ>> ይላል በግእዙ ሲጠቀስ

ጌታችን ከ5500 ዘመናት በላይ በዲያብሎስ ባርነት፣ በክፉ አገዛዝ ተይዘው በሲኦል በጨለማ ውስጥ ታሥረው የነበሩትን ሁሉ ወደ ገነት አስገባቸው። በመስቀሉ ዓለምን ሁሉ ሰላም አደረገ።

ለፍጥረቱ ሁሉ ፍጹም ድኅነትንና ፍጹም ነጻነትን ሰጠ።

**<< የምሥራች ደስ ይበላችሁ>> ማለት ነው።**

የምሥራቹም በለመለመ ቄጤማ (ሣር) አማካይነት ይካሔዳል። ምክንያቱም ልምላሜ ያለው ቄጤማ (ሣር) እንዲሁም ቅጠል የደስታ መግለጫ እንደሆነ በቅዱሳት መጻሕፍት በብዙ ክፍል ይገኛል።

ለምሳሌ፥ በዘሌዋውያን ብንመለከት፥ እግዚአብሔር ሙሴንና ሕዝበ እስራኤልን በየዓመቱ በለመለመው የዛፍ ቅርንጫፍ አማካይነት መንፈሳዊ የሆነውን የምስጋና እና የደስታ በዐል እንዲያደርጉ አዟቸዋል። ዘሌዋ 23፥39

በግእዙ ሲጠቀስ፥

**<<ነሥአ አብርሃም አዕፁቀ በቀልት ሰብሐ ወዘመረ በዕለተ ሰንበት>>**

የአማርኛ ትርጉሙም፥ አብሃም የሰሌን ዛፍ ዝንጣፊን ይዞ በሰንበት ቀን ፈጣሪው እግዚአብሔርን አመሰገነ ማለት ነው።

ቅዱስ ያሬድም በጣዕመ ዜማው አመሥጥሮታል።

**<<ድኅው ከሆሳዕና እዝል የተጠቀሰ ነው>>**

አዎ እነአብርሃም፣ ይስሐቅና ያዕቆብም የምስጋናንና የደስታን





በዐል በሚያደርጉበት ጊዜ ቀፅለ ልምላሜን መያዝ ያዘወትሩ እንደነበር ይታወቃል።

ከዚህ በላይ ከፍ ብሎ በቦታው (በሆሳዕና) እንደተገለጸው ጌታችን ወደ ቅድስት ሀገር ወደ ኢየሩሳሌም እንደመጣ በተሰማ ጊዜም ሕዝቡ፥ አረጋውያንና ወጣቶች፥ ሕፃናትም ጭምር የሰሌን ዛፍ ዝንጣፊን ይዘው፥ <<ሆሳዕና በአርያም ለወልደ ዳዊት ቡሩክ ዘይመጽእ በስመ እግዚአብሔር ወንጉሥሙ ለእስራኤል>> በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ በሰማይ ያለ መድኃኒት የዳዊት ልጅ፣ የእስራኤል ንጉሥ የተባረከ ነው በማለት በደማቅ ዕልልታና በልዩ ልዩ ምስጋና ተቀብለውታል።
ኢሳ 52፥1, 60፥1,መዝ 8፥2፥ እንዲሁም ዮሐ 12፥12 ጀምሮ እንመልከት

በተለይም ደግሞ በዘፍጥረት እንደምንመለከተው፥ በማየ አይኅ፥ ማለትም በኖኅ ዘመን የጥፋት ውሃ ዓለምን በሙሉ ባጥለቀለቀው ጊዜ ውሃው በምን ሁኔታ ላይ እንዳለ እንድታረጋግጥ ከመርከቡ ውስጥ በኖኅ የተላከችው በመንፈስ ቅዱስ የምትመሰለው ርግብ የጥፋት ውሃ መጉደሉን አረጋግጣ፥ ለምልክት ከለመለመ ሣር (ከቄጤማው) በጥርሷ ይዛ ወደላካት ወደ ኖኅ ተመልሳ የጥፋት ውሃ ጉደለ ደረቀ ብላ እንዳበሠረችው እንመለከታለን። ዘፍጥ 8፥6።

አዎ ከዚህ በላይ እንደተረዳነው በመንፈስ ቅዱስ የምትመሰለው ርግብ የጥፋት ውሃ መጉደሉን አረጋግጣ የጥፋት ውሃ ጉደለ፣ ደረቀ ብላ ለኖኅ እንዳበሠረችው። ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ደግሞ ይህንን ምሳሌ መሠረት በማድረግ፥ በግእዙ ሲጠቀስ <<ተሠዐረ ሞተ ኃጢአት>> ይላል የኃጢአት ሞት በክርስቶስ መስቀል ተሻረ፣ የጥፋትና የመርገም ማዕበል ጸጥ አለ፣ የፍዳና የኩነኔ ባሕር ደረቀ፥ ክርስቶስ በመስቀል ተሰቅሎ በአካለ ነፍስ ወደ ሲኦል ወርዶ ከ5500 ዘመናት በላይ በዲያብሎስ ባርነት በክፉ አገዛዝ ተይዘው በሲኦል በጨለማ ውስጥ ታሥረው የነበሩትን ሁሉ ወደ ገነት አስገባቸው። በመስቀሉ ዓለምን ሁሉ ሰላም አደረገ፥ ለፍጥረቱ ሁሉ ፍጹም ድኅነትንና ፍጹም ነጻነትን ሰጠ፥ የምሥራች ደስ ይበላችሁ እያለች የለመለመውን ሣሩን፥ (ቄጤማውን) እያደለች ሕዝበ ክርስቲያኗን የሕይወት ምሥራችን እያበሠረች ትገኛለች።

ይህን ያደረገልን እግዚአብሔር አምላካችን ይመስገን።

# ምዕራፍ 13፥

## ትንሣኤ (ፋሲካ) ትንሣኤ ክርስቶስ፥

ግእዝ፥ <<ክርስቶስ ተንሥአ እሙታን በዐቢይ ኃይል ወሥልጣን ዓሠሮ ለሰይጣን አግአዞ ለአዳም ሰላም እምይእዜሰ ይኩን (ኮነ) ፍሥሓ ወሰላም>>

አማርኛ ትርጉሙ፥ ክርስቶስ በታላቅ ኃይልና ሥልጣን ከሙታን ተለይቶ ተነሣ፣ ሰይጣንን ሻረው (በመስቀሉ ድል አደረገው)፣ አዳምን ነጻ አወጣው፣ ከእንግዲህ ወዲህማ ሰላም ይሁን፣ ከእንግዲህ ወዲህ ፍጹም ሰላም ሆነ ማለት ነው።

ትንሣኤ ክርስቶስ ወይም ፋሲካ ስንል፥ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ተሰቅሎ ዓለምን ያዳነበትንና በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ተለይቶ የተነሣበትን በማሰብ ከሌሎች ዐበይት በዐላት ለየት ባለ መልኩ የምናከብረው ዐቢይ በዐላችን ማለታችን ነው።

ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት የዘመረው ምስባክ በግእዝ ቋንቋ ሲጠቀስ፥

<<ወተንሥአ እግዚአብሔር ከመ ዘን̣ቃሕ እምንዋም
ወከመ ኃያል ወኅዳገ ወይን
ወቀተለ ፀሮ በድኅሬሁ>> ይላል።

ትርጉሙም፥ እግዚአብሔር ከዕንቅልፍ እንደሚነቃ ተነሣ፥ የወይን ስካር እንደተወው እንደ ኃያልም ሰው፥ ጠላቶቹንም በኋላቸው መታቸው። ይላልና፥ ጌታችን ሞትን ድል አድርጎ ከሙታን ተለይቶ ተነሥቷል። መዝ 77፥65።

በመሠረታዊ ትርጓሜው ምሥጢሩ ሲተነተንም፥
ትንቢቱ፥ እግዚአብሔር ከሰባ ዘመን በኋላ በረድኤት ተነሣ፣ እስራኤልን ጠላቶቻቸውን አጥፍቶ ከክፉ የባርነት ግዛት ነጻ አወጣቸው ማለት ሲሆን፥





ፍጻሜው ደግሞ፥

እግዚአብሔር መግነዝ ፍቱልኝ፣ መቃብርንም ክፈቱልኝ ሳይል በመስቀል ተሰቅሎ በሞተ በሦስተኛው ቀን ልክ ከዕንቅልፉ እንደሚነሣ ሰው ከሙታን ተለይቶ ተነሣ።

የወይን ስካር እንደተወው እንደ ኃያል ሰውም ሆነ።

የአዳምንና የሔዋንን፤ የሁላችንንም ጠላት የሆነውን ዲያብሎስን በመስቀሉ ድል አደረገ። መርገማችንን ሻረ፣ ዕዳችንንም ደመሰሰ፤ ዓለምንና የዓለምን ፍጥረት ሁሉ ነጻ አወጣ ማለት ነው።

በተጨማሪም ማቴ 28፥1, ማር 16፥1, ሉቃ 24፥1, ዮሐ 20፥11, 1ኛ ቆሮ15፥20 እና 1ኛ ጴጥ 1፥1 እንመልከት።

አዎ ነቢይ ዳዊት በ117፥24 መዝሙሩም፥
በግእዙ፥ <<ዛቲ ዕለት እንተ ገብረ እግዚአብሔር>>
እግዚአብሔር የሠራት ቀን ይህች ናት፣ ሐሤትን እናድርግባት፣ በእርሷም ደስ ይበለን ብሏል። (ዕለተ ሰንበትን ነው) ይኸውም ይህች ዕለተ ሰንበት እግዚአብሔር አምላካችን ከሙታን ተለይቶ የተነሣባት፣ ልዩ ልዩ ተአምራቱንም ያደረገባት ናትና በእርሷ ፈጽሞ ደስ ይበለን፥ የነፍስ ዕረፍት የመንፈስ ደስታ እናድርግባት ማለት ነው።

ፋሲካ ማለት ከግእዝ ወደ አማርኛ ቋንቋ በቀጥታ ሲተረጐም ደስታ ማለት ሲሆን፥ በአይሁድ ዘንድ ከጥንት ጀምሮ የተለመደ የነጻነት፣ የክብርና የደስታ በዐል እንደሆነ ይታወቃል። ሙሉ ምሥጢሩ በዓርብ ስቅለት ክፍል ገጽ 128 ስለተገለጸ ከዚያው እንመልከት።

በዐለ ፋሲካ (የፋሲካ በዐል) ስንልም፥ ጌታችን በመስቀል ተሰቅሎ መላውን ፍጥረቱ በማዳን ከሙታን ተለይቶ የተናሣባት ዕለት ስለሆነች መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በልዩ ልዩ ዝማሬ እያመሰገን የምናከብረው፥ ድኅነታችንና መንፈሳዊ ደስታችንን የምንገልጽበት በዐል፥ ሕዝበ እስራኤል የኤርትራን ባሕር በሰላም የተሻገሩባትን ዕለት በማስታወስ በዐላቸውን እንደሚያከብሩ ሁሉ፥

እኛም ከሞተ ኃጢአት ወደ ፍጹም ሕይወት የተሻገርንበትን በማሰብ፣ ይህን ያደረገልንን ፈጣሪአችንን በማመስገን የምናንጸባርቀው ልዩ የሆነ የምስጋና እና የመንፈሳዊ ደስታ በዐላችን ማለታችን ነው።

ስለ ሕዝበ እስራኤል የኤርትራን ባሕር በሰላም መሻገርና ነጻ መውጣት፣ ዘፀ 15፥1,12፥11, መዝ 135፥10፣ ስለ ፋሲካ በዐልም ማቴ 26፥1,ማር 14፥1, ሉቃ 22፥1, ዮሐ 12፥1, 13፥1 እንመልከት።

ትንሣኤ ደግሞ ተንሥአ ተነሣ ከሚል የግእዝ ግስ የሚገኝ ጥሬ ዘር ሆኖ፥ ቀጥተኛ ትርጉሙ ከተቀመጡበት ይሁን ከዕንቅልፍ ነቃ ብሎ መነሣት፥ በተለይም ደግሞ ከሞት ሕያው ሆኖ መነሣት፣ ከመቃብርም መውጣት ማለት ነው።

## ትንሣኤን፥ የሞት ሁኔታንና ስለ ጽድቅና ኃጢአት፣ ጻድቅንና ኃጥእንም፥ በመጥቀስ በሦስት ክፍል መድበን እንመለከተዋለን፥

ይኸውም፥

ሀ የፈጣሪ (የጌታችን) ሞትና ትንሣኤ፥

ለ የፍጡራን ሞትና ትንሣኤ፥

ሐ የሕያዋን ሞትና ትንሣኤ በማለት ነው።

## ክፍል 42፥

## ሀ የጌታችን ሞትና ትንሣኤ፥

የፈጣሪአችን፣ የጌታችን፣ የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ከፍጡራን ሞትና ትንሣኤ የተለየ ዐቢይ ምሥጢር ያለበት ነው።

የሰው (የፍጡር) ሞት ሳይወድ በተፈጥሮኣዊ ግዴታ በፈጣሪው ትእዛዝ የሚመጣ ሲሆን ቢሞትም መለኮታዊ አምላክ ሆኖ በራሱ ኃይልና ሥልጣን ሌላውን ፍጥረት ሊያድን አይችልም።

የጌታችን ሞት ግን በፈቃዱ ነው።

<<ሐመ በፈቃዱ ወተቀብረ በሥምረቱ ከመ ኪያነ ይርዳእ ወይቤዝወነ ወልድ ተንሥአ>>





ሊቁ ቅዱስ ያሬድ ቅዱስ መጽሐፉን መሠረት አድርጎ እኛን ለማዳን ሲል በፈቃዱ ታሞ ሞተ፣ በፈቃዱም ተቀበረ፥ በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሣ በማለት በጣዕመ ዜማው በልዩ ልዩ ክፍል እንዳመሠጠረው፥ ጌታችን ፍጥረቱን ለማዳን ሲል በፈቃዱ በለበሰው ሥጋ በፈቃዱ ተሰቅሉ ሞተ፣ ሞቱም ለፍጹም ሕይወት ነው። (ይህ ድጓ ሚያዝያ 24 ከጻድቁ ሊቡነ ተክለ ሃይማኖት እስመ ለዓለምም ይገኛል)

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስም በመልእክቱ እንደነገረን በእርሱ መቍሰል የእኛ ቍስል ተፈወሰ በእርሱም ሞት እኛ ዳን። እርሱ ተሰቅሉ ሞቶ ባያድነን ኑሮ ግን ሁላችንም ፍጥረቱ ለዘለዓለም ሕይወትን እናገኝም ነበርና ሞቱ ሕይወታችን ነው ማለት ነው። 1ኛ ጴጥ 2፥24

(አዎ የጌታችን ሞት ለሕይወት ነው)

በመስቀል ተሰቅሉ በሞተ በሦስተኛው ቀንም ሞትን አሸንፎ፣ መግነዙን ፍቱልኝ፥ መቃብሩንም ክፈቱልኝ ሳይል ከዕንቅልፍ እንደሚነቃ፣ የወይን ስካር እንደተወው እንደ ኃያል ሰው፥ ከሙታን በመለየት በገዛ ሥልጣኑ ብድግ ብሎ ተነሣ።

በትንሣኤውም ዓለምን አበራ፥ በትንሣኤው ሙታንን አነሣ፥ በትንሣኤው ልዩ ልዩ ተአምራትንም አደረገ፣ ፍጹም የሆነውንም ሕይወት ሰበከልን።

(አዎ የጌታችን፣ የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ከፍጡራን ትንሣኤ የተለየ ዐቢይ ምሥጢር ያለበት ነው)

ፍጡር ቢበቃም (ጻድቅም ቢሆን) በፈጣሪው በእግዚአብሔር ፈቃድ በተሰጠው ቃለ ኪዳን (ቃል ኪዳን) መሠረት የተወሰነውን ተአምራት ያደርጋል እንጂ መለኮታዊ አምላክ ሆኖ በራሱ ፈቃድና ውሳኔ አምላካዊ ሥራን ሊሠራ አይችልም።

ፍጡር ሲሞት በፈጣሪው ውሳኔ ይሞታል፣ ሲነሣም በእግዚአብሔር ኃይል ይነሣል እንጂ እንደ ፈጣሪ በራሱ ፈቃድና ሥልጣን ሊነሣ ከቶ አይችልም።

ጌታችን ግን የባሕርይ አምላክ፣ የፍጥረታት ሁሉ ባለቤት ሁሉንም ማድረግ የሚችል እንደ መሆኑ መጠን በራሱ መልካም ፈቃድ ሞቶ በራሱ መልካም ፈቃድ ተነሣ፣ ዓለምን ሁሉ አዳነ፥ ልዩ ልዩ አምላካዊ ሥራውንም ሠራ።

አዎ በማር 16፥12, በሉቃስ 24፥36 እና በዮሐ 20፥19 ጀምሮ በተመሳሳይ ተዘግቦ እንደምናገኘው ጌታችን ደቀ መዛሙርቱ ሐዋርያት በእርሱ ላይ እየደረሰ የነበረውን መከራ አይተው እኛንም እርሱን ያገኘ መከራ ያገኘናል ብለው ፈርተው ተደብቀው ወደ ነበሩበት ቤት ገብቶ፥ ቤቱ እንደተዘጋ በሩ እንደተቆለፈ በመካከላቸው ተገኝቶ ሰላም ለእናንተ ይሁን አላቸው በችንካር የተቸነከሩትን እጆቹንና በጦር የተወጋውንም ጐኑን አሳያቸው። ዓለምን ሁሉ ዞረው እንዲያስተምሩ አዘዛቸው።

ደቀ መዛሙርቱ ሐዋርያትም ከጌታችን ኃይልንና ጽናትን አግኝተው እንደበፊቱ ምንም ሳይፈሩ በጌታቸው በታዘዙት መሠረት አምላካዊ ሥራውን፥ መከራውን፥ ልዩ ልዩ ተአምራቱንና ንጹሕ የሆነውን ትምህርቱን ሁሉ ለመላው ዓለም አስተማሩ።

በመጨረሻም የጌታቸውን መከራ መስቀል ተሸክመው፥ ዓሠሩን በመከተል፣ በእምነታቸው ጸንተው፣ ሃይማኖታቸውን አስፋፍተው፥ ችግሩን፣ ፈተናውንና ተጋድሎውን ታግሠው ችለው፥ ዓለምንና የዓለምን ጣጣ ሁሉ በማሸነፍ በልዩ ልዩ መከራ በመንፈሳዊ ክብር አለፉ፣ ዓረፉ።

ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንም ይህን ምንም ያልተቀላቀለበትን ንጹሑ የክርስቶስ ትምህርት ከሐዋርያት እንሥቶ በሃይማኖታዊ ትውፊት (ቅብብሎሽ) ከአበው ተቀብላ አንድን ነገር ሳትቀላቅል ሕዝበ ክርስቲያኗን እያስተማረች ትገኛለች።

ይህ ከዚህ በላይ የተገለጸው የፈጣሪ (የጌታችን) ትንሣኤን የሚመለከት ሲሆን፥ ከዚህ ቀጥሎም የፍጡራን ሞትና ትንሣኤ ይገለጻል።

## ክፍል 43፥

## ለ የፍጡራን ሞትና ትንሣኤ፥

ፍጡር (ሰው) ፈጣሪው እግዚአብሔር እስከ ወሰነለት ዘመን ድረስ በዚሁ ጊዜያዊና ወቅታዊ በሆነ ዓለም ቢቆይም ባላወቀውና ባልጠበቀው ሰዓት ሳይወድ በግድ በፈጣሪው በእግዚአብሔር ፈቃድ በተለያየ ምክንያት በሞት ይጠራል። በጳውሎስ መልእክት 1ኛ ቆሮ ምዕራፍ 15፥22 እና ቍጥር 37፣ እንዲሁም በ1ኛ ተሰሉንቄ ምዕራፍ 4፥13 ጀምሮ በሰፊው





እንደተገለጸው፥ በአርአያ ሥላሴ የተፈጠረ ሰው ከሞተ በኋላም በጌታችን ምጽአት (በዓለም ፍጻሜ) ጊዜ ከሌሎች ፍጥረታት ተለይቶ በመነሣት እንደየሥራው የመጨረሻውን ፍርድ ከፈጣሪው ይቀበላል። እስከዚያም ጻድቃን በገነት፣ ኃጥኣን ግን በሲኦል ይቆያሉ። ሁለቱ ገነት እና ሲኦል የማቆያ ሥፍራ ናቸው ማለት ነው።

አዎ ገነት ማለት ለጻድቃን የተዘጋጀ ልዩ የሆነ መልካም ቦታ ሲሆን፥ ሲኦል ማለት ደግሞ ለኃጥኣን የተወሰነ የድቅድቅ ጨለማ ሥፍራ ነው። ዮሐ 5፥28, 2ኛ ቆሮ 5፥10

በመሆኑም ሕያዊት፥ ነባቢትና ለባዊት የሆነችው ነፍስ ስለማትሞት የመጨረሻ ፍርድ እስኪሰጥ ድረስ የጻድቃን ነፍስ በገነት፣ የኃጥኣን ነፍስም በሲኦል መቆየት ግዴታ ነው።

መንግሥተ ሰማያት እና ገሃነመ እሳት ግን እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ዝግ ሲሆኑ፥ ከመጨረሻው ፍርድ በኋላ ደግሞ ሁለቱ መንግሥተ ሰማያት እና ገሃነመ እሳት ተከፍተው ጻድቃን ከፈጣሪኣቸው የመጨረሻውን ፍርድ ተቀብለው ኑ ወደ እኔ ተብለው ወደ ዘለዓለማዊ ደስታ ወደ መንግሥተ ሰማይ ይገባሉ።

ኃጥኣን ደግሞ የመጨረሻውን ፍርድ ተቀብለው ወደ ዘለዓለም ሥቃይ፣ ወደ ዘለዓለም ልቅሶ ወደ ገሃነመ እሳት ሒዱ ይባላሉ።

ከዚህ በላይ በተጠቀሰው የቅዱስ መጽሐፍ መልእክት እንደምንረዳው ጻድቃንና ኃጥኣን በአንድ ጉድጓድ ውስጥ ቢቀበሩም እንኳ በሕይወተ ሥጋ እያሉ የሠሩትን የየራሳቸውን ሥራ (ግብር) ይዘው በመነሣት የመጨረሻውን ፍርድ ለመቀበል ወደ ፈጣሪኣቸው ይቀርባሉ እንጂ ጻድቅ የኃጥኡን፣ ኃጥእም የጻድቁን ሥራ ከቶ አይወስድም።

ይኸውም በአንድ እርሻ በሚዘራ ሁሉት ዓይነት እህል እንደሚመሰል ተነግሮአል።

ምሳሌውም፥ ሥንዴና ኑግ ተቀላቅሉ በአንድ እርሻ ቢዘራ፥ ሥንዴ ሥንዴውን፣ ኑግም ኑጉን ያፈራል እንጂ፥ ሥንዴ ኑጉን፣ ኑጉም ሥንዴውን አያፈራም ተብሏል።

ስለዚህ ሁሉም በሕይወተ ሥጋ እያለ በሠራው መሠረት እንደየሥራው ይቀበላል ማለት ነውና አሁን በሕይወተ ሥጋ እያሉ መልካሙን ሥራ መሥራት ያስፈልጋል።

እንግዲህ የፋሲካና የትንሣኤ ቀጥተኛ ትርጉምና ምሥጢሩ እንዴት እንደሆነ፥ እንደዚሁም የፍጡራንና የፈጣሪ ትንሣኤ ምንን እንደሚመስል ለመግለጽ ተሞክሯል።

በተጨማሪም 1ኛ ቆሮ 15፥22 እና ከቊጥር 37፣ እንዲሁም 1ኛ ተሰሎ 4፥13 ጀምሮ ሌሎችንም ቅዱሳት መጻሕፍትን በሰፊው እንመልከት፥

ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ የእኛ የሕያዋን ትንሣኤ ምንን እንደሚመስል እንመለከተዋለን፥

ሳንሞት እንነሣለን እንዴ ብንልም መልሱን በዚሁ እናገኘዋለን።

ከዚያ በፊት ግን የሚጠቀሱ ያሉት ተግባራት ሁሉ ጻድቅና ኃጥእ፥ (ጻድቃንና ኃጥኣን) በሚባሉ ሰዎች የሚከናወኑ በመሆናቸው ስለ ጽድቅና ኃጢአት፣ ስለ ጻድቅና ኃጥእ፥ እንዲሁም በብዛት ስለ ጻድቃንና ኃጥኣን በዐጭሩ እናብራራለን።

## ክፍል 44፥

## ጽድቅና ኃጢአት፣ ጻድቅና ኃጥእ፥

### ለመሆኑ ጽድቅና ኃጢአት ማለት ምን ማለት ነው?

ጽድቅ በቀጥታ ሲተረጐም እውነት ማለት ሲሆን፥ ጻድቃን ስንልም ለብዙ ሰዎች እውነተኞች ማለታችን ነው።

ጻድቅ ማለት እውነተኛ፣ የማይዋሽ፣ የእውነት ባለቤት የሆነው የእግዚአብሔር ወገን ማለት ነው።

ምክንያቱም በእግዚአብሔር ዘንድ ውሸት ስለሌለ እውነተኛ የእግዚአብሔር ሰውም እግዚአብሔርን ስለ ሚፈራ፣ በፍጹም ልቡ እግዚአብሔርን ስለሚያመልክ፣ እግዚአብሔርን ስለሚወድ ፈጽሞ አይዋሽም።





እንዲሁም ጻድቅ ማለት በዚሁ ምሥጢር ሲብራራ የጸደቀ ወደ መንግሥተ እግዚአብሔር (ወደ መንግሥተ ሰማይ) የሚገባ ማለት ነው።

ኃጢአት ማለት ደግሞ በቀጥታ ሲተረጐም ማጣት፣ ያጣ ማለት ሲሆን፥ ኃጥኣን ስንልም ለብዙ ሰዎች ያጡ፣ ኃጢኣተኞች ማለታችን ነው።

ምሥጢራዊ ትርጉሙም መንግሥተ እግዚአብሔርን (መንግሥተ ሰማያትን) ማጣት፣ ያጣ፣ ያጡ ማለት ነው።

ስለዚህም ትንሣኤ በሌላ መልኩ ሲተነተን ከዚህ በላይ በተገለጹት በጻድቃንና በኃጥኣን የሚከናወን ድርጊት ያለበት፥ የልብ፣ የሐሳብና የሥራ ትንሣኤ በሚል መንገድ ይገለጻል።

## ክፍል 45፥

## ሐ የእኛ የሕያዋን ሞትና ትንሣኤ፥

አዎ በአርአያ እግዚአብሔር የተፈጠረ ሰው በልቡ አስቦ ተነሥቶ በዕግሩ ተንቀሳቅሶ ሔዶ የተለያየ ዓላማ ያላቸውን ሁለት ዓይነት ሥራዎች ሊሠራ ይችላል።

ይኸውም፥

1ኛ የኃጢአት ተገዥ የዲያብሎስ ወገን የሆነ ክፉ ሰው በልቡ አስቦ ተነሣስቶ በእግሩ ተንቀሳቅሶ ሔዶ ይዋሻል፣ ክፉውን ነገር በመሥራት ሰዎችን ያጣላል፣ አባትንና ልጅን፣ እናትንና ልጅን ወንድምንና ወንድምን፣ እኅትንና እኅትን፣ ወንድምንና እኅትን ያጋጫል። በባለትዳሮችና በሚዋደዱት ሰዎች መካከል እየገባ ያለያያል፥ ከሃይማኖታዊ መልካም ምግባር ውጭ የሆነውን ሰይጣናዊ ሥራ ይሠራል። ክፉ ሰው በልቡ አስቦ ተነሥቶ በእግሩ ተንቀሳቅሶ ገሥግሦ ሔዶ በአርአያ እግዚአብሔር የተፈጠረውን ክቡሩን ሰው ገድሎ ንብረቱን ይዘርፋል።

በአጠቃላይ እግዚአብሔርንና ሰውን የሚያሳዝን ሰይጣናዊውን ተግባር ይፈጽማል።

ይህ ተግባር የኃጢአት ተግባር ነው።

ይህ ሥራ የኃጢአት ባለቤት የሆነው የሠይጣን ሥራ ነው። ይህንን ተግባር የሚፈጽም ሰው ኃጥእ (ኃጢአተኛ) ይባላል። ኃጥእ (ኃጢአተኛ) ማለትም ማጣት፣ ያጣ ማለት ነው። ምንን ያጣ ማለት ነው ብንልም?
መንግሥተ እግዚአብሔርን (መንግሥተ ሰማያትን) ያጣ ማለት ነው።

ይህንን ተግባር የሚፈጽም ሰው የሰይጣን ወገን ነው። የሰይጣን ወገን የሆነ ሰው በመጨረሻው የፍርድ ቀን ወደ ወገኑ ወደ ሰይጣን (ወደ ዲያብሎስ) ነው የሚሔደው። የሰይጣን ሥፍራ ደግሞ ገሃነመ እሳት ነው።

<u>2ኛ</u> የታደለው የክርስቶስ ተከታይ፣ የእግዚአብሔር ወገን የሆነው ሰው ግን በልቡ አስቦ፣ ከተቀመጠበት፣ ወይም ከተኛበት ሥፍራ፥

<u><<በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ>> በማለት በእግዚአብሔር ስም ተነሥቶ፥</u>

በእግሩ ተንቀሳቅሶ በመገሥገስ የእግዚአብሔር መመስገኛ ወደ ሆነችው ለስርየተ ኃጢአት ለመላው ዓለም ሰላም ሲል በቀራንዮ የተሰቀለው የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ወደሚፈተትባት ወደ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሔዶ፣ በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሆኖ እግዚአብሔር ያደረገለትን በጎ ነገር ሁሉ እያሰበ ፈጣሪውን ያመሰግናል።

<u>እውነተኛ ክርስቲያን፣ የክርስቶስ ተከታይ የሆነ ሰው፥</u> ጌታችን ስለ እኛ ፍጹም ሕይወት ሲል የተቀበለውን ልዩ ልዩ ፀዋትወ መከራ በልቡ እየተመለከተ እያለቀሰ ስለ ኃጢአቱ ስርየት ይጸልያል፥ ለበደሉ፣ ለጥፋቱ ይቅርታን ከፈጣሪው ይለምናል።

<u>እውነተኛ ክርስቲያን፣ የክርስቶስ ተከታይ የሆነ ሰው፥</u> ገነትን መንግሥተ ሰማያትን ያወርሰው ዘንድ ፈጣሪውን በጸሎትና በምስጋና ይማፀናል።

<u>እውነተኛ ክርስቲያን፣ የክርስቶስ ተከታይ የሆነ ሰው፥</u> የጽድቅ ዋና ማሰሪያ እውነተኛው ፍቅር ስለ ሆነ ራሱ ከሁሉም ጋር እየተፋቀረ ሌላውም ሰው ሁሉ እርስበርሱ እንዲፋቀር ከፍተኛውን ጥረት ያደርጋል።





<u>እውነተኛ ክርስቲያን፣ የክርስቶስ ተከታይ የሆነ ሰው፥</u> በተለያየ ምክንያት የተጣሉትን ያስታርቃል፣ የተራራቁትን ያቀራርባል በሰዎች መካከል የሚታየውን መለያየት በማስወገድ በሁሉም ዘንድ እውነተኛ አንድነት እንዲኖር ያደርጋል።

<u>እውነተኛ ክርስቲያን፣ የክርስቶስ ተከታይ የሆነ ሰው፥</u> የታሠረውንና የታመመውን ይጠይቃል የተቸገረውንም ባለው ዐቅም ሁሉ ይረዳል። በተለያየ ምክንያት ከእውነተኛው ሃይማኖቱ ወጥቶ በሌሎች አዳዲስ እምነቶች አካባቢ የሚደናገረውን ሰው እያስተማረ፣ እየመከረ ወደ ጥንታዊት ሃይማኖቱ ይመልሳል።

<u>እውነተኛ ክርስቲያን፣ የክርስቶስ ተከታይ የሆነ ሰው፥</u> በፍቅረ ንዋይ (ገንዘብን በመውደድ)፣ በጊዜያዊና በኃላፊ ጥቅም የሚሳሳተውን ይመክራል፥ ለጊዜያዊና ለኃላፊ ጥቅም ሲል ወገኑን የሚጎዳውን፥ በሐሜት፣ በተንኮል፣ በቅንዓት፣ በምቀኝነትና በመሳሰለው የጥፋት ጎዳና የሚሔደውን ሁሉ እያስተማረ፣ እየመከረ ወደ ጽድቅ ጎዳና ይመራል።

<u>በአጠቃላይ እውነተኛ ክርስቲያን፣ የክርስቶስ ተከታይ የሆነ ሰው፥</u> ሁሉም የሚጠቀምበትን መልካሙን ሥራ ይሠራል። እግዚአብሔርንና ሰውን የሚያስደስተውን በልቡ እያሰበ ያከናውናል።

<u>ይህስ የምን ሥራ ነው? ብንል</u>

<u>መልሱ የጽድቅ ሥራ ነው።</u>

<u>ይህ ሥራ</u> የጽድቅ ባለቤት የሆነው የእግዚአብሔር (የክርስቶስ) ሥራ ነው።

በክርስቶስ ክርስቲያን ተብሎ በተሰየመበት መሠረት ክርስቶስን እየተከተለ፣ የእግዚአብሔር ሕግንና መመሪያን እየጠበቀ፣ ትእዛዛቱንም እየፈጸመ የሚኖር፥ መልካሙን የጽድቅ ሥራ የሚሠራ ሰው ደግሞ ጻድቅ ይባላል። ጻድቅ ሰው ከራሱ አልፎ ሌሎችንም ይጠቅማል በጸሎቱም ብዙ ሥራን ሊሠራ ይችላል።

ለዚህም ከቅዱስ መጽሐፋችን ውስጥ ማስረጃ አለን፥ <u>ለምሳሌ ከያዕቆብ መልእክት ብንመለከት።</u>

<<እርስበርሳችሁ በኃጢአት ተናዘዙ፥ ትፈወሱም ዘንድ እያንዳንዱ ስለ ሌላው ይጸልይ የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይልን ታደርጋለችና ይላል>> <u>ያዕ 5፥16።</u>

እም ጻድቅ ሰው ከራሱ አልፎ ለሌላውም ሊያማልድ ይችላል ማለት ነው። ታዲያ እንደዚህ ያለ ጻድቅ ሰው በመጨረሻው የፍርድ ቀንስ ወዴት ይሔዳል? ያልን እንደሆን፥ መልሱ ወደ መንግሥተ እግዚአብሔር (ወደ እግዚአብሔር መንግሥት) ነው። የእግዚአብሔር መንግሥት ማለት ማን ናት? ብንልም መልሱ መንግሥተ ሰማይ ነው።

ስለዚህ ጻድቃን ተብለን ወደ መንግሥተ ሰማይ ለመግባት እንድንችል የጽድቅን ሥራ መሥራት አለብን ማለት ነው።

<u>እም ቅዱስ ጳውሎስ</u> ከዕንቅልፍ የምትነሡበት ሰዓት አሁን እንደደረሰ ዘመኑን እወቁ፤ ካመንበት ጊዜ ይልቅ መዳናችን ዛሬ ወደ እኛ ቀርቦአልና፥ ሌሊቱ አልፎአል ቀኑም ቀርቦአል፥ እንግዲህ የጨለማውን ሥራ አውጥተን የብርሃንን ጋሻ ጦር እንልበስ በማለት እንዳስተማረን። <u>ሮሜ 13፥11</u>

ጌታችን በመስቀል ተሰቅሎ አድኖናልና፥ በትንሣኤውም ፍጹም የሆነውን ብርሃኑን ሰጥቶናልና፥ መርገሙ፣ ፍዳው፣ ጨለማው ሁሉ አልፎአል።

በመሆኑም ይህን ያደረገልን አምላካችንን በልዩ ልዩ ዝማሬ እያመሰገን፣ በሰጠን የትንሣኤ ብርሃን ልንመላለስ ይገባናል። <u>ትንሣኤ ክርስቶስ</u> (ፋሲካ) የፈጣሪአችንን ፀዋትወ መከራ፣ ሞቱንና ትንሣኤውን፣ ቸርነቱንም ሁሉ እያስታወስን የምናከብረው ከሌሎች ዐበይት በዐላት የተለየ ክብርና መንፈሳዊ ታሪክ ያለበት፥ የጉዞዎች ሁሉ ዋና መዳረሻ፣ የሕይወት ተስፋዎች ሁሉ ማጠቃሊያ የሆነ ልዩ በዐላችን ነው።

<u>በተጨማሪም ከዚህ ቀጥለው ያሉትን ጥቅሶች እንመልከታቸው፥</u>

<u>1ኛ</u> እውነት እውነት እላችኋለሁ ሙታን የእግዚአብሔርን ልጅ ድምፅ የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል.......በመቃብር ያሉትም ሁሉ ድምፁን የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል፣ መልካም ያደረጉ ለሕይወት ትንሣኤ፣ ክፉውም ያደረጉ ለፍርድ ትንሣኤ ይወጣሉና በዚህ አታድንቁ። <u>ዮሐ 5፥25 ጀምሮ።</u>

<u>2ኛ</u> መልካም ቢሆን ወይም ክፉ እንዳደረገ እያንዳንዱ በሥጋው የተሠራውን በብድራት ይቀበል ዘንድ ሁላችን በክርስቶስ በፍርድ ወንበር ፊት ልንገለጥ ይገባናል። <u>2ኛ ቆሮ 5፥10</u>





<u>3ኛ ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል። (ይድናል) ዮሐ 11፥25</u>

<u><<ጥቅሶቹ ከአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ የተወሰዱ ናቸው>></u>

የጽድቅና የርኅራኄ ባለቤት እግዚአብሔር አምላካችን ይህን በፍጡር ሊለካና ሊገለጽ የማይቻል ቸርነቱን ሁሉ ስለ አደረገልን ለዘለዓለም የተመሰገነ ይሁን፥

በዐሉን የሰላም፣ የአንድነት፣ የፍቅርና የፍጹም ደስታ በዐል ያድርግልን

አሜን።

## <u>ምዕራፍ 14።</u>

## <u>ዕርገተ ክርስቶስ፥</u>

<u>የዕለቱ ምስባክ በግእዙ፥</u>

<<ዐርገ እግዚአብሔር በይባቤ፥
ወእግዚእነ በቃለ ቀርን፥
ዘምሩ ለአምላክነ ዘምሩ>>

<u>በአማርኛው ነጠላ ትርጉሙ ሲገለጽ፥</u>
እግዚአብሔር በመለከት ድምፅ ዐረገ፣ ዘምሩ ለአምላካችን ዘምሩ፥ እግዚአብሔር ለምድር ሁሉ ንጉሥ ነውና በማስተዋል ዘምሩ ይላል።

<u>በትርጓሜው መሠረት ተብራርቶ ሲነገር ደግሞ፥</u>
ጌታችን ከትንሣኤው በኋላ <u>40 ቀን</u> ለደቀ መዛሙርቱ ለሐዋርያት መጽሐፈ ኪዳንን፣ ሥርዓተ ሃይማኖትንና ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን ሁሉ ሲያስተምራቸው ሰንብቶ በተነሣ ባዓርባኛው ቀኑ በይባቤ መላእክት በቅዳሴ መላእክት፥ (በመላእክት ምስጋና)